# የእኩለ ሌሊት ወገግታ

The Resource Center
SIM International
P.O. Box 7900
Charlotte, NC 28241

ከ

## ወንድዬ ዓሊ

ቅጽ ሁለት

(ከ1934– 1966)

Wondiye Ali

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ታሪክ

ሚያዝያ 1992 ዓ.ም.

የእኩለ ሌሊት ወገግታ
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
(ቅጽ ሁለት ፤ ከ 1934 – 1966)

Copyright © 2000-KHC Literature
Department

# Awakening at midnight

Author - Wondiye Ali

(The Story of The Kale Heywet Church in Ethiopia)

(Vol.Two 1942 - 1973)

All rights reserved. No portion of this book may be reproduced in any form what so ever, except for brief quotations in reviews, with out the written permission of the publisher.

አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር በምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፥ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት በፍጹም የተከለከለ ነው። ለምርምር ሥራና ለጥናታዊ ጽሁፎች ማኅልበቻነት ከሆነ ግን ውሱን ሃሣቦችን ከመጽሐፉ ውስጥ መውሰድ የተፈቀደ ነው።

አሳታሚ፤ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት

የኮምፒውተር ሥራ፤ ውቢት ኑራሞ

Publisher: The Ethiopian Kale Heywet Church Literature
Department

Tel. 51 58 44 ስልክ 50 59 08
Fax. 251- 1 51 27 63

E-mail - AMKHC @ telecom.net.et
ፖ. ሣ. ቁ
P. O. Box 5829
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiopia

# ም ስ ጋ ና

በታሪክ ዋቢነታቸው ወይም በባለታሪክነታቸው ተመርጠው ቤተ ክርስቲያን ያለፈችበትን አስገራሚ የወንጌል ጉዞ ያለመታከት የተረኩልኝ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እጅጉን ባለውለታዎቼ ናቸው።

ከእኒህ አባቶች የቀዳሁት የሽበት ትዝታቸውን ብቻ ሳይሆን እውነተኛውን የነፍሳቸውን ወዘና እና አሻራ ጭምር ነበር። እነሱም ቢሆኑ የወንጌልን ተጋድሎ ከአንደበታቸው በተናገሩት ቃላት ብቻ ሳይሆን ከልቦናቸውም አንብቤ እገልጠው ዘንድ ሁለመናቸውን ሲይሳዩኝ ፍጹም ሳይሰስቱ ነበር። እንዲህ ባይሆን ኖሮ የሁለቱም የታሪክ መጻሕፍት አዘገጃጀት ሌላ መልክ በያዘ ነበር፤ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ይህንን የታሪክ መጽሐፍ ዝግጅት የመደበኛ ሥራቸው አካል አድርገው የይዘቱ አስተዋጽኦ እንዳይዛነፍ እንዲሟላም ስላደረጉት ጥብቅ ክትትል አመሰግናለሁ።

የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ማሞ ገብረ መስቀል ደርዝ ያለው የይዘት ግምገማ፥ ማበረታታትና ማደፋፈር በሚመጣው የሕይወት ዘመኔ የማልረሳው ትምሕርት ሰጥቶኛልና አመሰግናለሁ።

በጸሎትና በምክር ከጎኔ ያልተለዩኝን ቤተሰቦቼንና ወዳጆቼን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ እላለሁ።

## ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁን !

የድሮውን ዘመን አስብ፥
የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤
አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤
ሽማግሌዎችህን ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።

*( ዘዳግም 32:7–8)*

# ማውጫ

ገጽ

ጥቂት ቃል .............................. X
መቅድም .............................. XII
የአዘጋጁ ማስታወሻ .............................. XVI
1. መዳረሻ .............................. 1

## ምዕራፍ አንድ

የሽግግር ወቅት .............................. 21

- የቤተ ክርስቲያን መደራጀት .................. 28

3. ቀደምት ቤተ ክርስቲያናትና የኢትዮጵያ ወንጌላዊት
- የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ .................... 31

4. የሚስዮናውያን መመለስ .................... 39

5. ነባሩ የሃይማኖት ፖሊሲ .................... 53

- አፄ ኃይለ ሥላሴና ሚስዮናውያን ............ 65

## ምዕራፍ ሁለት

6. የጀማሪው ፍጻሜ.

- አሜሪካዊው ላምቤ .................... 79
- ኢትዮጵያዊው ላምቤ .................... 81
- ባይተዋሩ ላምቤ .................... 85
- የመጨረሻው ጽዋ .................... 91

7. የቋንቋዎች ተዛምዶ .................... 95

- የብርቱ አገልጋዮች መፍለቂያዎች .......... 102

## ምዕራፍ ሦስት

## በታላቅ መነቃቃት ታላቅ መስፋፋት (1940–1966)

8. የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ........................... 109

9. የቀዳማይ የወንጌል አገልጋዮች የስብከተ ወንጌል ስልት .. 112

## ምዕራፍ አራት

## መኀብኘት የሆነላቸው አውራጃዎች

10. ጎፋ፡–

- የጠፋው ልጅና የመጀመሪያው አማኝ ............. 137
- የማይሞተው ዘር ........................... 143
- አስገራሚው መገጣጠም ....................... 150
- እድገትና ስደት ............................ 169

11. ጋሞ፡–

- ትንሣኤ የሆነለት ሕዝብ ...................... 176
- ልዩ መኀብኘት ............................ 181
- የማያበራ ስደት ያልተናወጠ ጽናት .............. 189

12. ከምባ፡–

- የአቶ ጎሜ ግዛት ........................... 202
- ነጻ አውጭው ............................. 206

13. ዳውሮ ኮንታ፡–

- ምፅአተ ዳውሮ ............................ 223
- መልካም መንፈስ ያለበት ሰው ................. 231
- ሔራና ሴቃ .............................. 237

- ቦተሬ ቦንቤ ........................................ 237
- ውኃ በላ ውኃ ተፋ ! ........................................ 238

14. ቋሜ፦

- የሰናፍንጭ ቅንጣት ........................................ 243
- ማንነትና መደራጀት ........................................ 248

15. ሐመር ባኮ፦

- አኬት ቃል ........................................ 253
- እውነተኛው የሕይወት ቃል ........................................ 254
- እስራት – ነጻነት – ሰማእትነት ........................................ 256
- በዋጋ የተከፈተ በር ........................................ 267

16. ጌዴኦ፦

- በጨለመበት በራ ........................................ 273
- እውነተኛው ብርሃን ........................................ 278
- ባህል ዘለል ወንጌላውያን በጌዴኦ ........................................ 288
- ከደቡብ ወደ ደቡብ ጠረፍ ........................................ 290

17. በመጨረሻ ወደ መጀመሪያው፦

- ምዕራብ ኢትዮጵያ ........................................ 292
- ሰሜን ኢትዮጵያ ........................................ 295


## ምዕራፍ አምስት፤


18. ብሔራዊ አጀንዳ 1948 – 1966 ........................................ 303

19.የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር ........................................ 309

20. ሕጋዊ ሰውነት ........................................ 317

# ጥቂት ቃል

በእሾህ መሐከል የወጣች ጽጌረዳ ቀን ስትታይ ፈክታ፥ በብዙ ቀለም አምራ፥ አካባቢውን ስታውድ ማየቱ ልብን የሚያረካና መንፈስን የሚያድስ ነው። ያችው ጽጌረዳ ጨለማ ሲወርድባት ደብዝዛ፥ ቁሩ ሲያቆራምዳት፥ ስብር ስብርብር ብላ መዓዛዋን ያጣች–የሌለችም መስላ፥ እኩለ ሌሊት አልፎላት ጨለማው በብርሃን ወገግታ ተገፎ ፈካ ፈካ ስትል፥ እውድ እውድ ስታደርግና "አለሁ አለሁ" የሚል መልእክት ስታስተላልፍ ሰዎች ተጠግተው ሲያሸቷት፥ ቆርጠውም የቤት ማድመቂያና ጠረን መለወጫ ሲያደርጓት፥ ቋንቋዋንም ባናውቅ "ተመስገን ጌታዬ ለዚህ ያደረስከኝ እኩለ ሌሊቱን ወደ ብርሃን የለወጥክልኝ" ሳትል አትቀርም።

የስንዴ ቅንጣት መሬት ወድቃ፥ ተቀብራ፥ ዝናብ ወርዶባት፥ ጎርፍ አጥለቅልቋት፥ ጭቃው አጨቅይቷት፥ መኖርዋንና አለመኖርዋን ገበሬው አንዳንዴ እስከመጠራጠር ሲደርስ፥ ተስፋ ሲቆርጥ፥ እኩለ ሌሊቱ የክረምቱ ኃይል በበጋ ደምቆ፥ የበረዳት ሞቋት፥ በከርሰ ምድር ውስጥ የተቀመጠችው አንድ የስንዴ ቅንጣት ዘለላ ሆና ብቅ ስትል፥ ሰላሳም ስልሳም፥መቶም ከዚያም የበለጠ ፍሬ አፍርታ፥ ነፋስ ሽው ሲያደርጋት፥ ታጭዳ፥ ተወቅታ፥ ተፈጭታ፥ በከበረ ዕቃ ተቀምጣ፥ ከሞት ወደ ሕይወት ተለውጣ፥ ደካማዋ ለሰው ልጆች የብርታት ኃይልና ምንጭ መሆንዋ ከሚያስደንቀን የአምላካችን ሥራ አንዱ ነው።

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ቀን ጀምሮ የጨለማ ዘመን በፈረቃ የገጠማት ሲሆን፥ በውስጡ ግን በዝታለች፥ አድጋለች ጠንክራለች። "የእኩለ ሌሊት ወገግታ" ቅጽ ሁለት (1934–

1966) የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሌላ የመከራ ዘመን መኖሩን ቢያመላክትም በተጠቀሰው ዘመን ያጋጠማት ተግዳሮት ለየት ያለ መሆኑን አበክሮ ያስገነዝባል። ብላቴናዋ ቤተ ክርስቲያን ወራሪው ጠላት ወጥቷል፥ የሃይማኖት ነፃነት አገኘሁ፥ መንግሥታችን ተመልሷል፥ የምሥራቹን ቃል ያለ ስደት አውጃለሁ፥ እያለች ብትፈነድቅም፥ ያልተጠበቀ እኩለ ሌሊት ውስጥ ወዲያው ገብታ በስም ክርስቲያን ነን ከሚሉ ወገኖች ያልታሰበ መከራ ወረደባት።

የሐሰት ክስ፥ ፍትህ ማጣትና እሥራት የጥቂቶቹን ቅዱሳን ሕይወት ወደ ጌታ እንዲሄድ አፋጠነው። ይህም ቢሆን ወንጌል ወኅኒ ቤቶችን የዝማሬ ቦታ አደረገ፥ ሌባው ተለወጠ፥ ነፍሰ ገዳዩ ንስሐ ገባ፥ መንደሩ በምሥራቹ ቃል አዋጅ ተጥለቀለቀ፥ ድንበርም አልፎ እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጠለ፥ እንደ ደራሽ ወንዝ ሳይታወቅ ምድረ በዳውን አረሰረሰው። ጨለማው ተገፎ አካባቢው የሥጋ፥ የነፍስና የመንፈስ ብርሃን አገኘ።

በአንዳንድ አካባቢዎች " እግዚአብሔር በሰው መሐከል ወረደ" በማለት ሕዝቡ አፍ አውጥቶ መሰከረ። ቃልቻው፥ ባለውቃቢውና ጠንቋዩ በወንጌል እውነት ተማረከ። የምሥራቹ ቃል ነፃነትን እረፍትንና እፎይታን አወጀ። ሞታለች አብቅታለች የተባለችው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ፍሬ አፍርታ፥ መንፈስ ቅዱስ እፍ ብሎባት፥ የተበታተነው አካል በዝቶ ብቅ ስትል ያሳየን ዘንድ የእኩለ ሌሊት ወገግታ በዚህ መልክ ተጠናቅሮ ቀርቧል። መጽሐፉ ታሪክን ብቻ የሚገልጽ ሳይሆን ታሪክ የሠራውን ጌታ እግዚአብሔር አጉልቶ ያሚያሳይ ነው።

ደራሲው ወንድዬ ዓሊ እያንዳንዱ ታሪክ በተፈጸመበት አካባቢ በመሄድ እግዚአብሔርን በታሪኩ መሐከል እንዲያልፉ ያደረጋቸውን ሰዎች በማነጋገር ከምንጩ መረጃውን ለመሰብሰብ ያስቻለውን ጌታ

እያመሰገንን፥ ራሱን ለዚህ አገልግሎት በመስጠት ውርጩን፥ ዝናቡን ቆላውን፥ደጋውን እና እኩለ ሌሊቱን በመደብና በመሳሰሉት ቦታ እያሳለፈ የአምላካችን ድንቅ ሥራ ለሕዝበ ክርስቲያኑ በሙሉ ስላበሰረ ጌታ እግዚአብሔር ይባርከው። ወንድዬ ቅጽ ሁለትን ለመጻፍ ሲሯሯጥ ሰራቂው፥ ገዳዩና አጥፊው ዲያቢሎስ በመኪና አደጋ ሊጨርሰው ነካክቶት ነበር፤ መኪናው ከጥቅም ወጪ ስትሆን አንድ ሌላ አገልጋይ ወደ ጌታ ሄዱል፤ ወንድዬ ግን ታሪኩን መተረክ እንዲችል እግዚአብሔር ለዚህ አድርሶታል። እንዲህ ስላለው መስጠት እግዚአብሔር ይመስገን። ይህ ታሪክ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መኩሪያ ሳይሆን ስላለፈው በምሥጋና የሚሞላን ሆኖ፥ ታሪክን ጠቃሾች ብቻ ሳንሆን ቀጥሎም ታሪክን ለመሥራት የተዘጋጀውን ጌታ በዘመናችንም እንዲሠራ መጋበዙ የእርሱም ታሪክ ተካፋዮች እንድንሆን፥ ትኩስ በረከት እና ተሐድሶ ለማየትና ለመቅመስ እንድንችል፤ የሚያነቃቃን፥ የሚያነሳሳን እንደሚሆን አምናለሁ። መለስ ብለን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት ያበቃን እግዚአብሔር ይመስገን።

*ብርሃኑ ደረሰ*

*የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን*

*ሊቀመንበር*

ሚያዝያ 1992ዓ.ም.

# መቅድም

በምሕረቱና በጸጋው አቻና ወደር የሌለው የሰማይና የምድር አምላክ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ይህ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዝግጅት እንዲጠናቀቅ በመስኩ ለተሰማራው አገልጋይ መከናወንን ስለሰጠ ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ ይህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ በዚህ ሁኔታ ተዘጋጅቶ እንዲታተም ውሳኔ ያስተላለፈው በሐምሌ 1985 ዓ.ም. ነበር። ከዚያ ወዲህ በተደረገው ጥረትም ከ72 ዓመታት በፊት የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘፍጥረት ሲጀመር የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የዓይን ምስክሮች የሆኑ አረጋውያን እናቶችና አባቶች የተመለከቱትን፥ በጆሮአቸው የሰሙትን፥ በእጆቻቸው የዳሰሱትን የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል ለሚመጣው ትውልድ የሚያስተላልፉበት ታላቅ ቅርስ በሶስት ተከታታይ ቅጾች እንዲዘጋጅ በማድረግ ቤተ ክርስቲያኒቷ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አገልግላለች። ይህንንም ለማከናወን እንዲያመች ለጥናትና ምርምር የሚያግዙ በርካታ ሰነዶች በግዥ እና በውሰት እንዲሰበሰቡ እንዲሁም ታሪኩ በተፈጸመበትና ባለታሪኮቹ የሚገኙባቸው የአገሪቱ ማዕዘናትን ሁሉ ከሞላ ጎደል ያዳረሰ የብዙ ሺህ ኪሊ ሜትሮች ጥናታዊ የመስክ ጉዞ እንዲደረግ አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችታለች።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ድንቅ ስጦታዎች አንዱ የሆነው የጽሑፍ ጥበብ፦ ቀዳማይ የወንጌል አገልጋዮች በዘመናት አጥር ታጥሮ ውስን የሆነውን ሰብዓዊ እድሜ ተሻግረው ከሞት በኋላ የጊዜን ገደብ ሽረው፥ የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል እስከ ጌታ ዳግም ምፅአት ድረስ ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ እንዲናገሩ እንዲመሰክሩም

አስችሏቸዋል። ሌላ ምንም ምክንያት ሳይገኝባቸው በወንጌል በማመናቸው ብቻ ወደ መኳንቱና ገዢዎች የፍርድ ወንበር ፊት ሲጎተቱ፥ ወደ ወኀኒ ሲጣሉ፥ በአኮርባጅ ሲገረፉ፥ በዱላ ሲደበደቡ፥በሰደፍ ሲዳፉ፥ ደማቸው ፈሶ ሕይወታቸው ያለፈው እኒያ ቀደምት የወንጌል አርበኞች የፈሰሰው ደማቸው የወንጌል ዘር ሆኖ የዛሬውን ትውልድ አብቅሏል። እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለሰጡትም ምስክርነት የተገደሉ ሰዎች ነፍስ ከመሠዊያው በታች በታላቅ ድምፅ "ቅዱስና እውነተኛ የሁሉም የበላይ የሆንህ ጌታ ሆይ በምድር ባሉት ሰዎች የምትፈርደውና ስለ ደማችንም የምትበቀለው እስከ መቼ ነው ? "እያለ በመጮህ ላይ ነው( ራዕይ 9-10)

በትውልድ ተራችን የእግዚአብሔርን ወንጌል አደራ ተቀብለን የምንሮጥ ለእኛ እኒህን የሚያህሉ በዙሪያችን የከበቡን ምስክሮች ያሉን መሆኑን አውቀን፥ ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት እንሮጥ ዘንድ የሚያበረታታን ይሆናል።

እኒያ የቤተ ክርስቲያኒቱ በኩሮች በድቅድቅ የጨለማ ሥርዓት፥ በሰይጣንም ግዞት ታስረው ሳለ አስደናቂው የወንጌል ብርሃን ጨለማቸውን እንዴት እንደገፈፈላቸው የሚተርከው ይህ የእኩለ ሌሊት ወገግታ በሚል ርእስ የተዘጋጀው ቅጽ ሁለት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ታሪክ፦ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን፥ የሥነ መለኮት ተማሪዎችን፥ የታሪክ ተመራማሪዎች እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ትኩረት የሚስብ ዝግጅት እንደሚሆን ይጠበቃል።

የእኩለ ሌሊት ወገግታ ዓይነተኛ ጥንካሬው፥ ውበቱ፥ ጥራቱና ሞገሱ እንዲሁም ተአሚነቱ የሚመነጨው ጸሐፊው ባለታሪኮቹ ወይም ወራሲዎቻቸው ወይም ተተኪዎቻቸው በሚገኙበት ክልሎች እና የዳር አገሮች ሁሉ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን በመንዝ

መረጃዎችን አሰባስቦ እና አጠናቅሮ እንዲሁም በተለያዩ የማረጋገጫ ጥበቦች አገናዝቦ ሊተርከው በመቻሉ ነው። ጉዞው አድካሚና ከባድ መስዋእትነት የጠየቀ፥ ሥራውም ጽናትንና ትጋትን በእጅጉ የሚሻ ቢሆንም ወንድዩም እንደባለታሪኮቹ ሁሉ በነፍሱ ተወራርዶ በብቃት በትዕግሥትና በሐቀኝነት ተወጥቶታል። ለዚህ ያበቃው እግዚአብሔር አምላክ ነው፥ ስሙ ብሩክ ይሁን። አንባቢዎች ይህን የአምላካችንን ድንቅ ሥራ አገናዝበው እንዲማሩበትና ባለታሪኮቹም ትተውልን ያለፉትን አብነት ለመከተል እንዲችሉ በትሕትና እጋብዛለሁ። ዘላለማዊ የታሪክ ጻፍና ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ከዓይን ምስክሮችና በውስጡም ካለፉት ባለታሪኮች አንደበት የተተረከውን ይህን ዝግጅት ለብዙዎች በረከት፥ ለክብሩም መግለጫ ያደርገው ዘንድ ጸሎቴና ምኞቴ ነው።

*ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ መንግሥት ለአምላኩና ለአባቱም ካህናቱ እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን። (ራዕ 1:6)*

*ተስፋዬ ያዕቆብ (ዶ/ር)*

*የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን*

*ዋና ጸሐፊ*

# የአዘጋጁ ማስታወሻ

የእኩለ ሌሊት ወገግታ በሚል ርእስ የተዘጋጀው ይህ የታሪክ መጽሐፍ ከ1934 እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ገጽታ በተመረጡ የናሙና ትረካዎች መስተዋትነት ለማሳየት የተዘጋጀ ነው። " በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን " የተሰኘውና በ1990 ዓ.ም. የታተመው ቅጽ አንድ እትም ከ1920 እስከ 1933 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክ እንደሚዘግብ ያስታውሷል።

የሁለቱም ሕትመቶች ዝግጅት ዓላማ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን መጎብኘት፥ ቀዳማይ የወንጌል አገልጋዮችና ምእመናን ያለፉበትን አስገራሚ የክርስትና ሕይወት፥ ስለ እምነታቸውም የከፈሉትን ዋጋ እና ወንጌል በኃይልና በመንፈስ በተገለጠባቸው አውራጃዎች የተገኘውን ማኅበራዊ ፋይዳ ለአለውና ለሚመጣው ትውልድ ማስተላለፍ ነው።

ሁለቱን ቅጾች ለማዘጋጀት በአገራችን ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ቤተ መጻሕፍትን መፈተሽ፥ በአገር ውስጥና ውጭ በሚኖሩ ግለሰቦች እጅ የሚገኙ ተጠቃሽ መጻሕፍትንና መዛግብትን፥ የዕለት ሁኔታ መመዝገቢያ ማስታወሻዎችን፥የጥናት ወረቀቶችን፥ ማመልከቻዎችን እና ፎቶግራፎችን በግዥ እና በስጦታ በማሰባሰብ መመርመሩ የታሪኩ ቅንብር አንዱ ምንጭ ነው። የመጽሐፎቹ የመጀመሪያ ምዕራፎች እና መንደርደሪያዎች የተቀረጹትም ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች በመሆኑ አካልበ አንብቦ ለማለፍ አይመቹ ይሆናል።

ቋንቋውና አቀራረቡ የዝግጅቱን ዓላማና ተደራሲውን ያገናዘበ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። የእኩለ ሌሊት ወገግታ የሚዳስሰው በዋናነት የ33 ዓመት ታሪክ ቢሆንም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚገኘውን አንባቢ ሁለንተናዊ መረዳት ለማጎልበት ሲባል የዘመን አጥሩን በመጣስ እና ወደ ኋላ በማጣቀስ የሁኔታዎችን መነሻ እንዲመረምር መደላድሉን አመቻችቷል። የመጽሐፉን በርካታ ገጾች የሚሸፍነው እግዚአብሔር በገዛ ፈቃዱ ወገን ባደረገው ሕዝብ ሕይወት ውስጥ የተገለጠውን መንፈሳዊ ጉልበት በማያያዝም የተከተለውን ማሕበራዊ ተሐድሶ የሚተርከው ክፍል ነው። የእያንዳንዱ የአውራጃ ቤተ ክተክርስቲያን (በቀድሞ አጠራሩ ማሕበር) ታሪክ ከአንድ ልዩ ባሕርዩ ወይም ሥነ-ሰባዊ አሻራው ጋር እየተጣመረ በመተረኩ መልእክቱ ለባለ ታሪኩም ሆነ ለአንባቢ ስሜትና ልቦና ባዕድ እንዳይሆን ያደርገዋል ብሎ አዘጋጁ ያምናል።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እና የቀዳማይ የወንጌል አገልጋዮች ታሪክ ገና አልተቆነጠረም። የቤተ ክርስቲያናትን ድንበር በመላ እናካልል ብንል አቅምም ጉልበትም ስለማይበቃ በተወሰነ የዘመን ቅጽር ውስጥ የተወሰኑ አውራጃዎችን ብቻ ማየት ግድ ሆኖብናል። የቅጽ ሦስት የታሪክ መጽሐፍ( ኤሎሄ እና ሃሌሉያ 1966-1992 ዓ.ም.) ክፍተቱን እንደሚሞላው ይገመታል። ከእጁ የተቀበልነውን መልሰን ለቤተ ክርስቲያን እንድንሰጥ ያበቃን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን።

*የዛሬ መሠረት ትናንት ነው !*

*የነገ መሠረት ደግሞ ዛሬ ነው!*

*የትናንት፥ የዛሬና የነገ ባለቤት እግዚአብሔር ነው።*

*ይህም ታሪክ የዘመናት ባለቤት ለሆነው ለእግዚአብሔር ክብር*

*ለሰውም ጥቅም ተሰናድቷል።*

*መልካም ንባብ*

ቀጥሎም በሦስት ዙር የተከፈለ እና ወራትን የፈጀ ከአስር ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ በተሽከርካሪ በመጓዝ፥ ተሽከርካሪ በማይደርስባቸው አካባቢዎች በእግርና በጋማ ከብቶች በመሄድ በጠቅላላው 329 ዋቢዎችንና ባለታሪኮችን በማነጋገር ጆሮ ያልሰማቸው፥ ፀሐይ ያልሞቃቸውን መረጃዎችን በመሰብሰብ የዚህ ታሪክ አብይ አካል እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል።

በተዘዋወርንበት አካባቢዎች ሁሉ ቀዳማይ የወንጌል አገልጋዮች፥ አንጋፋ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ኹነኛ የማሕበረሰብ አውራዎች፥ የቀድሞ ሲራራ ነጋዴዎች፥ የቀድሞ ባሪያ ፈንጋዮች፥ የባላባት ወገኖች፥በወንጌል ኃይል አርነት የወጡ የቀድሞ ባለውቃቢዎች. . . ወዘተ፤ በሌላም በኩል በታሪክ ፊት ታሪክ የሌላቸው የሚመስሉ ገበሬዎች፥ የቀድሞ ገባሮችና ጪሰኞች፥ አንጥረኞች፥ ሸክለኞች የሸበት ትዝታቸው ከመቃብር በላይ ሕያው ሆኖ እንዲኖር ባላቸው ጥማት "ነፍሳቸውን እንኳን ሳይሰስቱ" የልባቸውን ጓዳ ጉዳንጉድ ሲያጫውቱን የታሪክ ንፍገት ያልጎበኛቸው መሆኑ በራሱ ታሪክ ነው። የዚህም ሆነ የፊተኛው መጽሐፍ ሽታ "ሰው– ሰው" "ሕይወት–ሕይወት" እንዲል የሚያደርገውም የእኒህ አረጋውያን ሕያው ምስክርነት ነው።

የታሪክ ማስረጃነታቸውን ለዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ከተረኩለት በኋላ በርካታ አባቶች የዚህን ዓለም ሩጫ ጨርሰው ወደ አምላካቸው እቅፍ መሰብሰባቸውን ስናጤን የታሪክና የጊዜ ጌታ የሆነውን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

የዚህ መጽሐፍ ተደራሲዎች በቅድሚያ በቤተ ክርስርቲያን ዙሪያ ያለው ሕብረተሰብ፥ ቀጥሎም ለግል እርካታ፥ ለጥናትና ለምርምር መዛግብትን የሚያገላብጠው ሁሉ እንደሚሆን ይገመታል። ስለሆነም

# 1. መዳረሻ

"የእኩለ ሌሊት ወገግታ የተሰኘውን" የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅጽ ሁለት ንባብ ከመጀመራችን በፊት፥ ለአንባቢው አእምሮ መደላድል ይሆነው ዘንድ ከቅጽ አንድ ይዘት አንዳንድ ነጥቦችን አስታውሰን ማለፍ ይገባናል፤ መነሻችንን ስናውቅ ያለንበትን ለማጤን፥ መድረሻችንን ለመተለም ያስችለናልና።

ስለ ኢትዮጵያ ክርስትናና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲነሣ አብዛኛው ወይንም ሁሉም ተራኪ አስቀድሞ የሚታወሰው እና ለዋቢነት የሚጠራው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጠቀሰውን ኢትዮጵያዊ ጀንደረባ ነው። ይህ ሰው በ34 ዓ.ም. ገደማ ክርስትናን ተቀብሎ ወደ አገሩ እንደተመለሰ ትውፊታዊና አፈ-ታሪካዊ ምንጮች ያስረዳሉ።[1]

በዚህ ሰው የክርስትና አቋም እና የእምነት ጽናት ሁለት አከራካሪ ነጥቦች ይጠቀሳሉ። ከፊሎቹ ስለዚህ ሰው ፍጻሜ መጽሐፍ ቅዱስ ስላልነገረን ወንጌልን ምን ያህል እንዳስፋፋ ደፍረን ለመናገር አንችልም፥ ሲሉ ገሚሶቹ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አቻኩሎ በፊልጶስ በኩል የተገናኘውን ሰው ያለፍሬ አይተወውም፤ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ወንጌልን ሳይመሰክር አልቀረም ይላሉ። ከእርሱ ሌላ ቅዱስ ማቴዎስን ለኢትዮጵያ የተሰጠ ሐዋርያ አድርገው የሚቆጥሩም አሉ። ሐዋርያው ማቴዎስ ወደ አክሱም መጥቶ ጥቂት ሰዎችን እንዳጠመቀ ወንጌልንም ሲሰብክ ኖሮ በዚያው አካባቢ ሰማእት ሆኖ እንዳለፈ የዘመነ ሮማ ገድለ ሰማዕታትንና የአዲስ ኪዳንን ቀኖና በመጥቀስ የዘገቡም ጥቂቶች አይደሉም።[2]

---

[1] . Ullen, Dorf E. The Ethiopians. 1966. p. 12
[2] . Aymro Wondem Agegnhu and J. Motovu, eds. The Ethiopian Orthodox Church. 1974 P.1

በተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች የተመዘገበው የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ የታሪክ ተመራማሪዎች " የሐበሻው ቆስጠንጢኖስ" ብለው በሚጠሩት በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት ነው። ለወንጌል መግባት ምክንያት የሆኑት ፍሬምናጦስና ሲድራኮስ የተባሉ ክርስቲያን ወጣቶች ምፅዋ ላይ ከተማረኩ በኋላ ወደ አክሱም ተወስደው የቤተ መንግሥት ባለሟል የመሆን ዕድል ማግኘታቸውና አጋጣሚውንም ለወን ጌል ምስክርነት ስለተጠቀሙበት ነው።

ፍሬምናጦስ ኋላ ላይ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (የሰላም አባት፥ የብርሃን ፈንጣቂ) በመባል የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሆኖ በእስክንድሪያው ጳጳስ በአትናቴዎስ የተሾመው ነው። የኢትዮጵያ ክርስትና ገና ከመጀመሪያው ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ተጣብቆ ዘመናትን ያስቆጠረበትም መነሻ ይህ አጋጣሚ ነው።

የኢትዮጵያ ክርስትና በቆዳ ስፋት አንጻር አብይ መስፋፋት ያደረገው በ451 ዓ.ም. በተደረገው የኬልቄዶኑ ጉባኤ ተወግዘው በ480 ዓ.ም. ግድም ወደ ኢትዮጵያ በገቡት ዘጠኝ መነኮሳት አማካኝነት ነው።" ተሰዓቱ ቅዱሳን " በመባል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት የሚሰጣቸው እኒህ መነኮሳት መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ከግሪክና ከአረማይክ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉመዋል። በዘመናቸው ከሥነ-ጽሑፍ ጋር በተዛመደ መልኩ የሥነ-ጥበብ ዕድገት እንደነበረም ይወሳል።

የኢትዮጵያ ክርስትና በቤተ መንግሥት ዙሪያ ተጀምሮ ወደ ሕዝብ ለመውረድ ሲፍገመገም የመኖሩን ያህል በረዥም ዕድሜ ታሪኩ ከማእከላዊ መንግሥት ግዛትና ኃይል መስፋፋት ጋር በተጓዳኝ ሲሰፋ፥ የመንግሥቱ አቋም ርዶ ድንበሩ ሲጠብ እንዲሁ የክርስትናም ዳርቻ ሲሰበሰብ ኖረ።

አልፎ አልፎ ግን ከመንግሥት ተጽእኖ የጸዱ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቶች ወንጌልን ወደ ደቡብና ወደ ደቡብ ምዕራብ ግዛቶች

በማዳረስ ረገድ የማይናቅ ጥረት አድርገዋል። በተለይም ሐዲስ ሐዋርያ በመባል የሚታወቁት አባ ተክለሃይማኖት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለተደራጀ ሐዋርያዊ ተልዕኮ ዋና ተጠቃሽ ናቸው። አባ ተክለሃይማኖት በ1215 ዓ.ም. በቡልጋ አውራጃ ምድረ ጽላልሽ በተባለ አካባቢ የተወለዱና የደብረ ሊባኖስን ገዳም የመሠረቱ፥ እንዲሁም ደቡብ ኢትዮጵያን በተለይም ወላይታንና ዙሪያዋን በወንጌል ለመድረስ ብዙ የጣሩ፥ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትንም የተከሉ " የበቁ " ሰው ናቸው።

ከልማዳዊውና የብሕትውና ይዘት ካለው የወንጌል ስርጭት ባፈነገጠና ወንጌላዊ ወደ ሆነው እምነት የተራመደ የጎላ ስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ የተደረገው በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ( 1434–1468 ) ሲሆን ጀማሪውም በምንኩስና ስሙ እስጢፋኖስ በመባል የሚታወቀው የትግራይ ተወላጅ ነበር። እንቅስቃሴው ደግሞ ከመሥራቹም ስም ተቀራኝቶ ደቂቀ እስጢፋ ይሰኛል።

የእስጢፋኖስ ተከታዮች በመንፈሳዊ እውቀታቸው በሳል በመሆናቸውና የእደጥበብ ሙያ መውደዳቸው ከሌላው ምእመን የተለዩ አድርጓቸው ነበር። በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል እንደተመዘገበው “ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም” ስላሉ እንደ መናፍቃን ተቆጠሩ። በካኅናቱ ቀስቃሽነትና በንጉሡ ሸንጎ ቀርበው ሕዝቡ በሞት እንዲቀጡ በየነባቸው። በመጨረሻም አፍንጫቸውን ተፎንነው ምላሳቸውን ተቆርጠው በድንጊያ ተወግረው ሞቱ።

መሪያቸው እስጢፋኖስም ለማርያም፥ ለመስቀልና ለንጉሥ ባለመስገዱ የቀረበበትን ክስ ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሰ እንዲሟገት ጠይቆ ዕድል ሳይሰጠው ሥርዓተ ንግሣቸውን በአክሱም ሊያካሂዱ በሄዱት በአፄ ዘርዓያዕቆብ ትዕዛዝ ወደሸዋ ( ተግዞ) እንዲመጣ ተደረገ። የንጉሡ ወታደሮች የእጆቹን ቆዳ ገፍፈው፥ አሰቃይተው፥ በእስር ጣሉት፤ በዚያም ሕይወቱ አልፋለች። የደቂቀ እስጢፋ እንቅስቃሴ በዚህ ሁኔታ

ከተዳፈነ ከአንድ መቶ ዓመታት ያህል በኋላ ነበር የምዕራብ አውሮፓው የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የጀመረው።

በዚያች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ አይነቱ መነቃቃትና የወንጌል ሥራ ሳይቋረጥ በሙላት ተካሂዶና ሥነ መለኮታዊ ይዘቱ በሚገባ ተቀርጾ እንዲሁም በሕይወት መታደስ ላይ አትኩሮ ቢሆን ኖሮ በነፍስም በሥጋም አገራችንና ሕዝባችን ከአሁኑ በተሻለ አቋም ላይ በተገኙ ነበር የሚለውን ግምት ብዙዎች ይጋሩታል።

# ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ

በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ዓላማ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሚስዮናውያን ነበሩ። ከፊሎቹ ለእውነተኛው የወንጌል ተልእኮ የመጡ ሲሆን የቀሩቱ ደግሞ ዓለማዊና ግላዊ ስውር ዓላማ ለማስፈጸምና ለመፈጸም የገቡ እንደነበሩም ታሪክ አውስቶታል።

ቀዳሚው የፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ከአውሮጳው ተሐድሶ ከ100 ዓመት በኋላ በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ( 1625–1660 ) ነው። ይህ ፋና ወጊ ጀርመናዊ የወንጌል መልዕክተኛ ፒተር ሄይሊንግ ይባላል። ፒተር ሄይሊንግ በ1644 ዓ.ም. ወደ አገሩ ለመመለስ ግብፅ እንደደረሰ ቱርኮች ሃይማኖቱን እንዲክድ ሲያስገድዱት አሻፈረኝ በማለቱ አንገቱን በሰይፍ ቀልተው ገድለውታል።

ፒተር ሄይሊንግ ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየበት ወቅት የዮሐንስ ወንጌልን ወደ አማርኛ በመተርጎሙ በቅዱሳት መጻሕፍት የአማርኛ ትርጉም ታሪክ ፈር ቀዳጅ ሥራ እንዳከናወነ አያጠያይቅም።

ከፒተር ሄይሊንግ ህልፈት ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ ጀምስ ብሩስ የተባለው ተመራማሪ የጥቁር አባይን መነሻ ምንጭ ለማግኘት በ1760ዎቹ ያደረገውን አሰሳና የጎንደርን ታሪክ በ1782 ዓ.ም. በመጽሐፍ አሳትሞ ለንባብ በማብቃቱ አውሮጳውያን በተለይም ሚስዮናውያን እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ልባቸው ተነሣሣ።

በ1824 እ.ኤ.አ. የአራቱ ወንጌላት የአማርኛ ትርጉም ታትሞ በመውጣቱ የእንግሊዝ Church Missionary Society (CMS) የተባለው ድርጅት መልእክተኞቹን አስማርቶ ወንጌላቱን በኦርቶዶክሳውያን ዙሪያ ለማሰራጨት እቅድ ነደፈ። ለዚህም ተልዕኮ ሳሙኤል ጎባት እና ክርስቲያን ኩግለር ለሚስዮናዊነት ተመረጡ፥ ወደ ኢትዮጵያም ጉዞ ጀመሩ።

ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አስቀድሞ የተነሣው ክርስቲያን ኩግለር በሚያዚያ ወር 1818 ዓ.ም. ግብፅ ደረሰ፥ ከአምስት ወር በኋላ ሳሙኤል ጎባት ተቀላቀለው። ሁለቱ ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ የሚዘልቁበትን መንገድ ሲያሰላስሉ ሁለት ኢትዮጵያውያን መልእክተኞች ግብፅ ገቡ። አንደኛው መልእክተኛ ወልደጊዮርጊስ የተባሉ መነኩሴ ሲሆኑ ሌላው ደግሞ ስማቸው ያልተጠቀሰ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ ናቸው። እኒህ መልእክተኞች ወደ ግብፅ የሄዱት በትንሹ ራስ ዐሊ ዘመነ ምስፍና ሲሆን ዓላማውም በጎንደር ቤተ መንግሥት ዘንድ ሞገስ የተነሣቸውን አቡነ ቄርሎስን ( ከ1808/09 እስከ 1822/23 ዓ.ም. ጳጳስ የነበሩ ) አገልግሎት የሚተኩ ሌላ ጳጳስ ለማምጣት ነበር። ተልእኮው ያልተሳካላቸው መነኩሴው አባ ወልደ ጊዮርጊስ እዚያው ግብፅ እያሉ በጠና ታመሙ፤ በአጋጣሚ የተዋወቋቸው ሳሙኤል ጎባትና ክርስቲያን ኩግለር የህክምና ርዳታ አደረጉላቸው። በዚሁ መነሻ ጥሩ ወዳጅነት መሠረቱ። በአባ ወልደ ጊዮርጊስ አነሳሽነትም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የኢትዮጵያን ገዳም ለመጎብኘት በሶርያ በኩል ወደ እስራኤል አገር ረዥም ጉዞ ተጓዙ። በኢየሩሳሌም ሃያ አምስት ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን አግኝተው ጥልቅ የሆነ ወዳጅነትን አተረፉ። ሁለቱ ሚስዮናውያን የአማርኛ ቋንቋ በጥሩ ሁኔታ አጠኑ የአበሻን ምግብ ጣዕም አጣጣሙ፤ ከሁሉም በላይ በመነኮሳቱ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ተመሰጡ።

ጎባትና ኩግለር በነሐሴ ወር 1819 ዓ.ም. ወደ ካይሮ ተመለሱ፥ በዚህ ወቅት ደግሞ የትግሬው ገዢ የደጃዝማች ሰባ ጋዲስ መልእክተኞችን ማግኘታቸው መንገድ መሪ የማጣታቸው ጉዳይ ተቃለለላቸው። የደጃዝማች ሳባ ጋዲስ መልእክተኞች ወደ ካይሮ የመጡበት ምክንያት ለአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን የጣሪያ መክደኛ ቆርቆሮ ለመግዛት፥ ጳጳስ

ለመውሰድ እና ለእንግሊዙ ንጉሥ ለጆርጅ 4ኛ ደብዳቤ ለማድረስ ነበር። የደጃዝማቹ ዋና መልእክተኛ ዐሊ ኡመር ለ17 ዓመታት ያህል የትግራይ ደረ የነበረና ዊሊያም ኮፊን የተባለ እንግሊዛዊ ባልደረባ ተሰጥቶት ነበር። ኮፊን ግን ካይሮ ከደረሰ በኋላ የቀድሞ አለቃው ከነበረውና በጊዜው የእንግሊዝ ቆንስላ ከሆነው ሰው ጋር ሲገናኝ ራሱን እንደ ዋና ልዑክ ዐሊ ኡመርን እንደ ባልደረባው አድርጎ በማቅረቡ ጭቅጭቅ ተፈጠረ።[3] ኮፊን ኩግለርን ይዞ ወደ እንግሊዝ ተሻገረ፤ እሱ በዚያው ሲቀር ኩግለር ተመልሶ መጣ። የደጃዝማቹን ደብዳቤ ለማድረስ ሦስት ዓመት ያህል ፈጀ ማለት ነው።

ከዚህ ሁሉ ትዕግሥት በኋላ ጎባትና ኩግለር በዐሊ ኡመር መሪነት አዲግራት ደረሱ፥ ደጃዝማቹ ታላቅ መስተንግዶ አደረጉላቸው። ጎባት ተግባቢና ብልህ በመሆኑ ተቀባይነቱ የተሻለ ሲሆን ኩግለር ግን በጠባዩ ብዙዎች የሚደሰቱበት አልነበረም። ነገር ግን የጠባዩ አስቸጋሪነት በህክምና አዋቂነቱ በርካታ ሰዎችን ይረዳ ስለነበር በዚሁ ተካክሶለታል።

ሁለቱ ሚስዮናውያን በጎንደርና በትግራይ ሕዝብና አብያተ ክርስቲያናት መካከል በአማርኛ የታተሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አሰራጭተዋል። ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በ1823 ዓ.ም. ኩግለር ለአደን በወጣበት ገጠር በአደጋ ሲሞት ጎባት ግን ወደ ጎንደር አለፈ። ትዕግሥትና ብልሃት በተሞላው መንገድ ለእጨጌ ፊልጶስ፥ ለመሥፍኑ ለደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም፤ ሥልጣንና ጉልበታቸውን በመሣፍንቱ ተቀምተው በስም ብቻ ንጉሠ ነገሥት ለነበሩት ለአፄ ጊጋር፥ እንዲሁም ለጎንደር አድባራት አለቆች ሁሉ የአራቱ ወንጌላትን የሐዋርያት ሥራ እና የሮሜ መልእክቶችን ለማሰራጨትና የወንጌልንም ምስጢር ለመስበክ በቅቷል። በጊዜው ከነበረው የእግዚአብሔር ቃል ረሃብ የተነሣ የአገሬው ሰዎች በተለይ አራቱን ወንጌሎች በእጅ እየገለበጡ ያባዙት እንደነበር ታውቋል።

ሳሙኤል ጎባት ከሦስት ዓመት የተሳካ አገልግሎት በኋላ በ1825 ዓ.ም. ወደ አገሩ ተመልሶ በ1826 ዓ.ም. ኢዘንበርግ ከተባለ ጀርመናዊ ጋር

---

[3] . Aren Gustav. Evangelical Poneers in Ethiopia. 1978. P. 50-51

እንደገና ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ሆኖም የጤና መታወክ ስለገጠመው በ1829 ወዳገሩ ተመለሰ። ኢዘንበርግም ቢሆን ተቃውሞ ስለበዛበት ዘግይቶ መጥቶ ከቱጎዳኘው ባልደረባው ከክራፍ ጋር የረባ ሥራ ሳይሠሩ በ1830 ወደ ግብፅ ተመለሱ።

ሳሙኤል ጎባት ከአስር ዓመት በኋላ በ1837 በኢየሩሳሌም የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሆነ። ክራፍ ግን በ1831 ኢዘንበርግን ጨምሮ ወደሸዋ መጣ። በጊዜው የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ስላሴ ዕደ ጥበብ አስተማሪና የእጅ ባለሙያ እንጂ ሃይማኖት ሰባኪ የሚፈልጉ ሰው ስላልነበሩ የሚስዮናውያኑ እንቅስቃሴ የተገታ ነበር።

ክራፍ በሸዋ በቆየበት ወቅት ስለኦሮሞ ሕዝብ በቂ እውቀት አካበተ፥ ቋንቋውን አጠና። " ይህንን ሕዝብ በወንጌል መድረስ ቢቻል መላ አፍሪቃን ለማገልገል እንደሚቻል" ጽኑ እምነት አደረበት።[4]

ክራፍ ለኦሮሞዎች ልዩ ስሜት ያሳደረበት ከብዙ ዓመታት በፊት ባልተጻር ቴሌዝ ( Balthazar Tellez ) የተባለ ፖርቱጋላዊ ኦሮሞዎችን ከጀርመን ነገዶች ጋር እያነጻጸረ፥ ስለጀግንነታቸው፥ ስለ ብዛታቸው የጻፈውን መጽሐፍ በማጥናቱ ነበር።[5] ንጉሥ ሣህለ ስላሴ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወይም ለማስገበር ሲዘምቱም አብሮ እየዘመተ በኦሮሞዎች መካከል በመገኘት በርካታ መረጃዎች አጠናቀረ።

እ.ኤ.አ. በ1858 በጀርመን አገር በአሳተመው የጉዞ ማስታወሻው "እግዚአብሔር ሆይ ጋሎችን ብትሰጠን መላው ማዕከላዊ አፍሪቃ ለእኛ ይሆናል!" በማለት በርካታ ሰዎችን የሚያነሳሳ ጽሑፍ ጻፈ።[6] የእኛ ጀርመን ለአውሮጳ የሆነችውን ያህል ኦሮሞችም ለአፍሪቃ እንዲሁ ናቸው ሲልም አከለበት።[7] ይህም የብዙ አገልጋዮችን ልብ አቀጣጥሎ ለወንጌል

---

4. አማኑኤል አብርሃም፥ የመካነ ኢየሱስ ቤ.ክ. አጀማመር፥ 1987 ዓ.ም. ገጽ 15 ።
5. ዝኒ ከማሁ፣14–15
6. Aren, Gustav. 1978 p 103
7. አማኑኤል አብርሃም 1987 ገጽ 15

አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ቢያነሣሣም በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በነበረው ተከታታይ የውስጥ ጦርነቶች ሳቢያ ሳይሳካላቸው ዓመታት አሳለፉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጡት ሚስዮናውያን መካከል ታሪክ የሚያስታውሰው ሌላው የሚስዮናውያን ቡድን በእንግሊዛዊው ማርቲን ፍላድ የሚመራው "መናኝ ሚስዮናውያን"(The Piligrim Missionaries) የተባለውና በግንቦት ወር በ1848 ዓ.ም. የገባው ቡድን ነው።[8] እንደ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት አፄ ቴዎድሮስ ለእደ ጥበብ ባለሙያዎች እንጂ ለውጭ አገር ወንጌል ሰባኪዎች እምብዛም ክብር ስለ አልነበራቸው ሚስዮናውያኑ በጎንደር አካባቢ ያሉትን ፈላሻዎች ወንጌል እየሰብኩ ያመኑትን ግን በኦርቶዶክስ ሥርዓተ ጥምቀት እንዲያጠምቁ ፈቅደውላቸው ነበር።

በተጨማሪም እነዚህ ሚስዮናውያን ደብረታቦር አጠገብ ጋፋት በሚባል ቦታ ከንጉሡ ትንሽ መሬት ተሰጥቷቸው የቀለምና የሙያ ትምህርት ቤት ከፍተው ማሠልጠን ጀምረው ነበር። በየሰንበቱ ግን በአካባቢው ባሉት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እየሄዱ አብረው ያመልኩ፥ ለተራው ምእመን ወንጌልን በአማርኛ ይሰብኩ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ያሰራጩ። የአፄ ቴዎድሮስ መዋዕለ ዜና ጸሐፊ የነበሩትና በ1852 ዓ.ም. ወንጌልን የተቀበሉት ደብተራ ዘነብ የጋፋቶች የመጀመሪያ ወንጌላዊ እንደነበሩም ታውቋል።[9]

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓይነተኛ ተሐድሶ ለማምጣት ዓላማው አድርጎ የተነሣው "የመናኝ ሚስዮናውያን" ጥረት ፍጻሜው በእስረኝነትና ለቴዎድሮስ መድፍ ፋብሪካ የብረት አቅላጭ መሆኑ አሳዛኝ ድምዳሜ ነው። ከቴዎድሮስ የጦር መሣሪያ ፍላጎት በተጨማሪ

---

[8] Aren, Gustav. 1978 p. 90
[9]. Ibid p. 93

በማያገባቸው እየገቡ ለአሳዛኙ ድምዳሜ አስተዋጽኦ ያደረጉት ሚስዮናውያንም ታሪክ ክፉኛ ይወቅሳቸዋል።[10]

አፄ ቴዎድሮስ በእስር የተጣሉትን አውሮጳውያንና ሚስዮናውያንን ለማስፈታት በመጣው የእንግሊዝ ጦር ላለመማረክ ራሳቸውን ከገደሉ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት "የመናኝ ሚስዮናውያንን" አገልግሎት ለማስቀጠል ማርቲን ፍላድ በ1867 ዓ.ም. በመተማ በኩል ተመልሶ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱን ፈቃድ ጠይቆ ነበር። በወቅቱ በፈላሻዎች መካከል ወንጌልን ተቀብለው የተጠመቁ 44 ያህል ሰዎች እንደነበሩ ታውቋል። አፄ ዮሐንስ ግን ሚስዮኑ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ፥ ለፈላሻ አማኞችም ዕውቅና ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።[11]

አፄ ቴዎድሮስ በ1860 ዓ.ም. በመቅደላ አምባ ከመሰዋታቸው በፊት ከ1858 ዓ.ም. አንስቶ ምፅዋ ገብቶ በመስፈር የማእከላዊ ኢትዮጵያን ዙፋን ዕድል ፈንታ ሲጠባበቅ የነበረው የስዊድን የወንጌል ተልዕኮ ( Sewidish Evangelical Mission ) ጥረት ሌላው ታሪክ የሚያስታውሰው ታላቅ ተልዕኮ ነው።

ወቅቱ ዋግሹም ጎበዜ ( አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ) ፥ ደጃች ካሣ ( አፄ ዮሐንስ ) እና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ለኢትዮጵያ መንግሥት የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን እየተፎካከሩ ወይም ጦርና የጦር ሰው እያሰባሰቡ ያሉበት ዘመን ነበር። ሚስዮኑ ምፅዋ አጠገብ የእምኩሉን ጣቢያ መሥርቶ በኩናማዎች መካከል ወንጌልን እያስተማረ ወደ መሐል አገር በተለይም ወደ ኦሮሞዎች ዘንድ ዘልቆ ወንጌልን የሚሰብከበትን አመቺ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር። ሚስዮኑ እምኩሉ በከፈተው ትምህርት ቤት ውስጥ ከትውልድ መንደራቸው በባሪያ ፈንጋዮች እየተፈነገሉ ለባርነት ባህርማዶ ሊሻገሩ የተዘጋጁትን የኦሮሞ ወጣቶች መልሶ

---

10. ዳኘው ወ/ሥላሴ፥ የእስራት ዘመን በአበሻ አገር፥ (ትርጉም) ፥ 1963፥ ገጽ 48–49 ።

11. Aren, Gustav. 1978 p 103

በመግዛት( በመዋጀት ) ለወንጌላዊነት ያስለጥናቸው ነበር። ከባርነት ከተዋጁት መካከል አናሲሞስ ነሲብ በቀዳሚነት በመጋቢት ወር 1864 ( ማርች 31 ቀን 1872 ) ተጠመቁ። [12] በቀጣዩ ዓመት ህዳር 22 ቀን 1865 ዓ.ም. አናሲሞስና ከኦርቶዶክስ ወደ ወንጌላዊት እምነት የመጡ ሦስት ተማሪዎች ከሌሎች ሚስዮናውያን ጋር ቅዱስ ቁርባን ተካፈሉ።

ቄስ ሉንዳል ያቺን ማኅበር " ቤቴል ቤተ ክርስቲያን" ብለው ሰየሟት። ይህች ማኅበር ነች የኤርትራ ወንጌላዊት እና የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስን የወለደችው። [13]

እነዚህ ከባርነት ተዋጅተው የወንጌል እምነትን የተቀበሉትና ከኦርቶዶክሳዊነት ወደ ወንጌላዊነት የፈለሱት ኢትዮጵያውያን ለሚስዮናውያን ዝግ የነበረውን በር ሁሉ እያለፉ ወንጌልን በመሐል አገርና በምዕራብ ኢትዮጵያ ለማሰራጨት እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል። ሚስዮናውያን በሃያኛው ክፍለ ዘመን አዲስ ስትራቴጂ ቀይሰው፥ ከመንግሥታት ተደራድረው፥ በይፋ፥ መጥተው፥ እምነት ከማስፋፋታቸው በፊት ወንጌል ወደ ጅማ እና ወለጋ የገባው በእነዚህ የአገር ተወላጆች አማካኝነት እንደሆነ ልብ ይሏል።

---

12 . Ibid p. 165

13 . Ibid p. 167

# የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ



*የመጀመሪያዋ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ( ጸሎት ቤት) ሲዳማ፥ሆማቾ 1925ዓ.ም.*

ከ1900 ዓ.ም. አንሥቶ የአሜሪካን ፕሬስቢቴሪያን ሚስዮን መልእክተኛ በመሆን በደቡብ ምሥራቅ ሱዳን ሲያገለግሉ የነበሩት ዶ/ር ቶማስ ላምቤ በኢትዮጵያ ውስጥ በቅድሚያ የሕክምና፥ ቀጥሎም የወንጌል አገልግሎት የሚሰጡበት በር በድንገት ተከፈተላቸው። ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ዘልቀው በሳዮ ጣቢያ እንዲመሠርቱ የጋበዟቸው በወቅቱ የወለጋ

ጠቅላይ ግዛት አገረ ገዢ የነበሩት ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል ናቸው። ራስ ብሩ ዶ/ር ላምቤን እንዲጋብዙ ያስገደዳቸው በሺህ በሚቆጠሩት ወታደሮቻቸው መካከል የተነሣው ወረርሽኝ ጥቂት የማይባሉትን የሠራዊቱን አባላት በመፍጀቱ ነበር። በሳዮ ግቢያ ያበረከቱት አገልግሎት ከራስ ብሩ ወልደገብርኤል ሌላ፥ ራስ ናደው አባወሎ፥ ደጃዝማች መሸሻ እና ደጃዝማች ይገዙ ከተባሉት በጊዜው ተሰሚነት ከነበራቸው ሹማምንትና መኳንንት ጋር ወዳጅነትን አተረፈላቸው። እነዚህ ሰዎች በተፈላጊው ቦታ፥ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ እየተገኙ ዶ/ር ላምቤን እስከ መጨረሻ ድረስ እንዲንከባከቡ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሰዎች ሆነው ተገኝተዋል።

ዶ/ር ቶማስ ላምቤ ኢትዮጵያ ሲመጡ በዙፋን ላይ ተቀምጠው የነበሩት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ሲሆኑ፤ አልጋወራሹና የመንግሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተፈሪ መኮንን ነበሩ።

ዶ/ር ላምቤ ከአልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን ጋርም የነበራቸው ወዳጅነት እንዲህ ቀላል አልነበረም። በ1914 ዓ.ም. ላምቤ ለእረፍት ወደ አሜሪካ ሲሄዱ ለዚያን ጊዜው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለሐርዲንግ የአልጋወራሹን ደብዳቤ ይዘው ለመሄድም ታማኝነትን አግኝተው ነበር። በ1915 ዓ.ም. ከአሜሪካ ሲመለሱ ዛሬ የፓስተር ኢንስቲትዩት የሚባ ለውን (ቀድሞ የላምቤ ሆስፒታል የሚባለውን የሕክምና ማዕከል) አቋቋሙ። ከ1919 በኋላ ላምቤ ለደቡብና ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ወንጌልን ለማድረስ ሸክም አደረባቸው። ከነሸክማቸው ለሁለተኛ ዙር እረፍት ወደ አሜሪካ ሄዱ። ወቅቱም እግዚአብሔር የደቡብ ኢትዮጵያን የወንጌል ታሪክ የቀየሰበት መነሾ ሆነ።

ዶ/ር ላምቤ በአሜሪካ ቆይታቸው “ አቢሲኒያን ፍሮንቲየር ሚሽን” የሚባል የሚስዮን ድርጅት አቋቋሙ። ድርጅታቸውን በ1893 ዓ.ም. ከተመሠረተውና “ ሱዳን ኢንቲሪየር ሚሽን ” ከሚባለው ሚሲዮን ተቋም ጋር አጣምረው በ1920 ዓ.ም. ከባለቤታቸው፥ ከሴት

ልጆቻቸውና ከሌሎች ስምንት ሚስዮናውያን ጋር ወደ ኢትዮጵ° ገቡ። በዚሁ የአሜሪካን ፕርስቢቴሪያን ሚስዮን አባልነታቸው አከተመ።

እግዚአብሔር በአሜሪካ፥ በአውስትራሊያ፥ በኒውዝላንድና በካናዳ የነበሩትን አገልጋዮች ወደ አፍሪቃ ለወንጌል ተልእኮ እንዲመጡ መንፈሳቸውን በሚያነቃቃበት በዚያ ወቅት ከ1900 በኋላ በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ አውራጃዎች አዋጅ ነጋሪዎች እና ጎዳና ጠራጊዎች ተነሥተው ነበር። በነዚያ አዋጅ ነጋሪዎች አማካኝነት የደቡብ ኢትዮጵያ ነዋሪ ሕዝብ የወንጌሉ ዘር የሚቀበልበት የልቡ ማሣ ለስልሶ ነበር። በዚህ በእግዚአብሔር ልዩ አሠራር ቀዳሚ ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል ኤሣ የሚባል ባህላዊ ትንቢተኛ በጋሞ፥ በወላይታ፥ በቁጫ፥ በቦረዳ፥ በጎፋ ለሕዝቡ መንፈሳዊ መታደስ እንደሚሆንለት ይተነብይ ነበር።

አንዳንድ ትንቢቶቹ ዝርዝር ሁኔታዎችንና ምልክቶችን ያገናዘቡ ጭምር ነበሩ። ኤሣ ከሚያስተላልፈው ትንቢት ሌላ ጠንካራ ግብረገባዊ ትምህርቶችንም ያስተምር ነበር። ከዚህም የተነሣ እስከ ክፍለ ዘመኑ አጋማሽ ድረስ የነበሩና የእድሜ ባለ ጠጋ የሆኑ አባቶች ስለእምነታቸው ሲጠየቁ " በኤሣ ሃይማኖት ሕግ ሥር ነን" ማለትን ያዘወትሩ ነበር።

ከኤሣ ሌላ አባዬ በከምባታና ሃዲያ፥ ጨለኬ በጎፋ አውራጃ፥ አታራ ገመዶ በጌዶኦ፥ ቢካማ ጎልጎ በሲዳሞ ( ቢዮ) አካባቢ ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ትንቢቶችን እያወጁ የሕዝቡን ሥነ ልቦናና መንፈስ ማስናዳታቸው ለብዙዎች የእግዚአብሔር ሰዎች ምስጢር ሆኗል።

ዶ/ር ቶማስ ላምቤና የሚስዮኑ አባላት ዲሴምበር 25 ቀን 1927 እ.ኤ.አ. ወይም ታህሳስ 16 ቀን 1920 ዓ.ም. ጅቡቲ ደርሰው በባቡር ወደ ኢትዮጵያ ምድር አለፉ። ሕጋዊ የወንጌል ስብከት ፈቃድ ለማግኘት ደጅ ሲጠኑ እስከ የካቲት መጨረሻ ድረስ በአዲስ አበባ ቆይተው በብላቴን ጌታ ኅሩይ ምክርና እገዛ " አየር ለመቀበል" በሚል የተሸፋፈነ ፈቃድ የካቲት 28 ቀን 1920 ( ማርች 7 ቀን 1928 እ. ኤ. አ ) መድረሻቸውን ጅማ አድርገው ከአዲስ አበባ ሠፈራቸው ከጉለሌ ተነሡ።

በዶ/ር ላምቤ ጥንቃቄ ገና ከአሜሪካ ሳይነሡ የታለመው የጉዞ አቅጣጫ በእግዚአብሔር ጥንቃቄ፥ በመለኮታዊ አሠራሩ ተለውጦ (ተቃንቶ) ወደ ጅማ የሚያደርሰውን መንገድ ስተው ቀጥታ ወደ ደቡብ አመሩ። በያዙት መንገድ ጅማ እንደማይደርሱ ያወቁት ግን ከቀናት መዘግየት በኋላ ነበር።

በልባቸው ጅማን አርግዘው በእግራቸው ሆሣዕና ደረሱ፥ ቀጥሎም ወላይታ፥ ከዚያም ከፊሎቹ ወደ ሲዳማ አለፉ። ዶ/ር ላምቤም በወለጋ ተዋውቀዋቸው የነበሩትን ወዳጆቻቸውን ደጃዝማች መሸሻን በሆሣዕና፥ ደጃዝማች ይገዙን በወላይታ፥ ራስ ብሩን በሲዳማ አገኙ። ሁሉም ሹማምንት በየግዛታቸው ውስጥ ሐኪም ቤት፥ የቀለምና የሙያ ትምህርት ቤት እንዲከፍቱ ጋበዙአቸው። ቀስ በቀስም ወደ ጅማ ለመሻገር የማለማቸው ነገር ሟሸሸ። በሦስቱ አውራጃዎች የሚስዮን ጣቢያዎች ለመመሥረት ደፋ ቀና ማለት ጀመሩ።

ጊዜው የኢትዮጵያ መንግሥት በውስጥ ተቃርኖ የተወጠረበት፥ አንዱ መሥፍን ከሌላው አይሎ የአንዱን ግዛት ሌላው ለመጠቅለል የሚራኮቱበት፥ በሌላ በኩል ደግሞ የመሳፍንቱን ኃይል አዳክሞ ሥልጣንን ወደ ማእከላዊ መንግሥት ለመሰብሰብ በየአንጻሩ ከፍተኛ ትግል የሚካሄድበት ጊዜ ነበር። በሌላ አንጻር ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት ዙሪያ “ፀረ- ነጭ” ስሜት ያቆጠቆጠበት ወቅት ስለነበር[14] መጋቢት 23 ቀን 1921 ዓ.ም. ይፋ የሆነ የሥራ ፈቃድ ከውጭ ጉዳይ ምኒስትሩ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በጽሑፍ እስከሚደርሳቸው ድረስ ይህ ነው የሚባል የተቀናጀና የጎላ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ቀርቶ የየአካባቢ ሹማምንት ፊት ነስተዋቸው ሲዋከቡ ነበር ዓመቱን ያሳለፉት።

---

14. ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ፥ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ አንደኛ መጽሐፍ፥ 1965 ገጽ 131-132።

ከፈቃዱ መገኘት በኋላ በሲዳማ ሆማቾ፥ በሃዲያ የላምቡዳ እና የማረቆ ጣቢያ ተመሠረተ፤ በወላይታ የኦቶና ጣቢያ ተጠናከረ። የወንጌል ዘር ተበተነ።

1923ዓ.ም. ከመገባደዱ በፊት ከየጣቢያዎቹ የማይሞተው የወንጌል ዘር በአስገራሚ ሁኔታ የመብቀሉ የምሥራች ተሰማ። በወላይታ የኩሎ ኮንታው ተወላጅ አቶ ብሩ ዱባለ በወጣትነታቸው የሰሙትን የወንጌል ቃል አጸኑ። አቶ ዋንዳሮ፥ አቶ ደስታ፥ አቶ ጎዳና፥ አቶ ግንጃ፥ አቶ አሬቦ፥ አቶ ኩና ኮባ፥ አቶ ወልዴ፥ አቶ ጮራሞና ባለቤታቸው ወ/ሮ ፖካሬ፥ የአቶ ደስታ ባለቤት ወይዘሮ ዲያሚ እና ሌሎችም በወንጌል ኃይል ተማረኩ።

በሲዳማም አቶ ገነሜ ሑንዴ የተባሉ የቤተሰብ ኃላፊ የመጀመሪያው የሲዳማ የወንጌል አማኝ ሆኑ፤ ቀጥሎም አቶ ሆሼ፥ አቶ ጋኖቤ፥ አቶ አርቲሳ፥ አቶ ፋቴሳ፥ አቶ ባለሞ በአንድ ሰሞን አመኑ።

በከምባታና ሃዲያ (ላምቡዳ) ጣቢያ ፈረንጆች የ1923 ዓ.ም. የገና በዓላቸውን ለማክበር አንድ ሳምንት ያህል ሲቀራቸው የመጀመሪያው የሃዲያ አማኝ "የያኔው ወጣት ሰብሮ ወሰሮ" ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ። ሰብሮ ወሰሮ ወይም በፈረስ ስማቸው አባዱጊሶ ካመኑ ከሁለቱ ቀናት በኋላ አቶ ሽጉጤ ዳዳ ክርስትናን ተቀበሉ። ከእነዚህ ከሁለቱ ሌላ ቱለሮ፥ ባቦ፥ ሻፊሶ የሚባሉቱ ባመኑት ላይ ተጨመሩ። በማረቆ አቶ ደምበል ገና ሚሲዮን ከመግባቱ አስር ዓመት ያህል ቀደም ብሎ በግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን ሲመረምሩ ለተገለጠላቸው የወንጌል እውነት የተገዙ እንደነበሩ በጊዜው የነበሩት ሚስዮናውያን አረጋግጠዋል። በጠቅላላው በመጀመሪያው ሁለት ዓመት አገልግሎት ሰላሳ ያህል ሰዎች በወንጌል እንደአመኑ ታውቋል። እኒህ ከሰላሳ የማይበልጡት ናቸው ለዛሬዋ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፥ 4,288 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እና ከ4,000,000 በላይ ለሚገመተው ምእመን መነሻ የሆኑት።

# መስፋፋት

ዶ/ር ላምቢ በተገኘው ውጤት ተዘናግተው ሳይቀመጡ በ1923 ዓ.ም. በደጃዝማች በየነ መርድ ጋባዥነት የጎፋን ጣቢያ ከፈቱ። በዚህ ጣቢያ ከአምስት ዓመት በኋላ በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም. ሳካ፥ ሳንኩራ እና ሲምብሩ የተባሉ ሰዎች የውሃ ጥምቀት ወስደው ነበር፥ በስሙት ወንጌል እስከ መጨረሻ አልጸኑም እንጂ።[15] ያልተጠመቁ ሌሎች ያመኑ ሰዎችም እንደነበሩ ታውቋል።

በዚያው ዓመት የጅማ ጅሬን ጣቢያ ተከፈተ። ይህኛውም ቢሆን በአምስት ዓመት አገልግሎቱ በአፍላው የጣሊያን ወረራ ወቅት ሰባት ሰዎችን ለማስጠመቅ በቅቶ ነበር ፍጻሜአቸው ግን አልታወቀም።

በ1925 ዓ.ም. የካቲት ወር የዱራሜ ጣቢያ ሥራ ጀመረ። በዚሁ ዓመት ሰኔ ወር ለጉጂና ለጌዴኦ ሕዝብ ወንጌል ለማድረስ አመቺ ነው የተባለው የቱቲቲ ጣቢያ ተከፈተ። ከአንድ ዓመት በኋላ በ1926.ዓ.ም. ሚስዮናውያኑ ወደ ጋሞ ዘመቱ። በመጀመሪያ ጨንቻ ቀጥሎም ሾማ ላይ ሰፈሩ። ወደ ሰሜን ኢትዮጵያም ለመስፋፋት ሙከራ የተደረገው በዚሁ ዓመት ነበር። የሚስዮን ጣቢያ እንዲመሠረትባቸው በቅድሚያ የታሰቡት ቦታዎች ላስታ ላሊበላ እና ደብረ ማርቆስ ነበሩ።

በ1927ዓ.ም. ዶ/ር ቶማስ ላምቢ የኢትዮጵያዊነት ዜግነት መብት በፈቃዳቸው ተቀዳጁ። ኢትዮጵያዊ ዜግነት መቀበላቸው መሬት በኮንትራት ለመያዝ የሚያበቃቸውን ሕጋዊ መብት አሳጣቸው። ስለዚህም በ1927 ዓ.ም. በጣሊያን ወረራ ዋዜማ በላሊበላ ግንባታ ተጀመረ። እኒህ አገሬው "ታቦት የሌላቸው ሰባኪዎች" የሚላቸው ባይተዋሮች ፅኑ ኦርቶዶክስ በሆነው ኅብረተሰብ ውስጥ ፋይዳ ያለው ሥራ ሳይሰሩ የጣሊያን ወረራ ተከተለ፤ የሰሜን ኢትዮጵያ የወንጌል ሥራም ተጨናግፎ ቀረ።

---

[15] አቶ ሶሳ ጋይላ እና ወንጌላዊ ዮሐንስ ዳርታ፥ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥ ነሐሴ 1 ቀን 1989 ዓ.ም. ሽፍቲ ባንዳ ጎፋ።

# መከራ

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያ ጥምቀት የተፈጸመበት ቀን ታህሳስ 16 ቀን 1925ዓ.ም. ( ዲሰምበር 25 ቀን 1932 )ሲሆን በታውም ሆማቾ (ሲዳማ )ነበር። ተጠማቂዎቹ ደግሞ አራት የአገሬው ተወላጆች ነበሩ። የጥምቀቱን ስነ ስርዓት የፈጸሙት ዶክተር ላምቤና ሚ/ር ኬይን እንደነበሩ ታውቋል። ሚስዮናውያኑ ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ልክ በአምስተኛው ዓመት የመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች መጠመቃቸው ምን ያህል አድካሚ አገልግሎት እንደሰጡ ይመሰክራል።

ሁለተኛው ዙር ጥምቀት የተደረገውም በዚያው በሲዳማ ሲሆን ሐምሌ 22 ቀን 1925 ዓ.ም. በሚ/ር ዳፍ አማካኝነት ሦስት ሰዎች ተጠመቁ።

ሦስተኛውና በጥሩ ጥንቃቄ ታህሳስ 1 ቀን 1926 የተፈጸመው ጥምቀት የተካሄደው በወላይታ ነበር። በዕለቱ ከብዙ አማኞች መካከል ክርስቲያናዊ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስምንት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ተጠመቁ።

አራተኛው ዙር የጥምቀት ሥነ ሥርዓት የተፈጸመው በከምባታና ሃዲያ ነበር። የመጀመሪያው የሃዲያ ተወላጅ ተጠማቂ የሆነው አቶ ኢያጎ ባምቦሬ ሚያዚያ 14 ቀን 1926 ዓ.ም. በላምቡዳ ጣቢያ ቢጠመቅም ኗሪነቱ ግን አዲስ አበባ ነበር። በዚሁ በላምቡዳ ጣቢያ ከአንድ ዓመት በኋላ ከሃያ ሁለት አማኞች መካከል ለመጠመቅ ፈቃደኛ የሆነው የሁለተኛው ዙር ተጠማቂ ሌሬሶ ቄቆ የሚባል ሰው ብቻ ነበር።

ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ሥራው ዘግይቶ በተጀመረባቸው በታዎች በጎፋ በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም. ሦስት ሰዎች ተጠመቁ። በጅማ በ1928 ነሐሴ ወር ላይ አራት ሰዎች በ1929 ዓ.ም. መጀመሪያ ደግሞ ሌሎች አራት ተጠመቁ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ሚስዮናውያኑ ከኢትዮጵያ ተጠቃለው እስከወጡበት ጊዜ ድረስ በአዲስ አበባና አስቀድሞ ጥምቀት

በተካሄደባቸው ቦታዎች ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም የተጠመቁ ሌሎች ሰዎች ነበሩ።

ከ1920 ዓ.ም. አንስቶ እስከ 1929 ዓ.ም. የኤስ.አይ. ኤም ሚስዮን በአስራ አምስት የሰበካ ጣቢያዎች ዘጠና ሁለት ሚስዮናውያንን አሰማርቶ ለዛሬይቱ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነ የወንጌል ሥራ አከናውኗል። በጥረቱም በጠቅላላው አንድ መቶ ያህል ሰዎች የክርስቶስን አዳኝነት የወንጌልን እውነት ሊቀበሉ ችለዋል። የተጠመቁት ብዛት ግን ግማሽ ያህሉ ብቻ ነበር። የሲዳማ፥ የወላይታ፥ የከምባታና ሃዲያ የሰበካ ጣቢያዎች ከሞላ ጎደል የቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ይዘው ነበር።

ሚስዮናውያን በጣሊያን ጦርነት አስገዳጅነት ከአገር ከወጡ በኋላ ምንም እንኳን በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያለው መሪ አስልጥነውና ተከተው ባይሄዱም እንኳን መንፈስ ቅዱስ ባነቃቃቸውና ባነሳሳቸው የአገሬው ተወላጆች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እጅግ አስደናቂ የሚባል የወንጌል ስርጭት ተደረገ።

ፋሽስቶች በዘመኑ ከነበረው ዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን አሰላለፍና ፖለቲካዊ ሂደት በመነሳት ሁሉንም ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ከአገር እንዲወጡ ሲያስገድዱ በአገር ተወላጆቹ የወንጌል አማኞች ላይ የስደትና የመከራ እሳት አቀጣጠሉ።

በዚህ የመከራ ጎዳና ውስጥ እያለፉ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጊዜ በመቶ የሚቆጠሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ለመትከልና በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ምእመናንም ለማስተባበር የበቁ እንደወርቅ የነጠሩ እንደብረት የጠነከሩ የወንጌል አርበኞች የተነሱት ሚስዮናውያን ከወጡ በኋላ ነበር (ለዝርዝሩ ቅጽ አንድን ይመልከቱ። )

በ1933 ዓ.ም. የጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያ አርበኞች ድል አድራጊነት ሲደመደም ስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ አገልግሎቷን ወደ አደባባይ አወጣች። መስተዳድሩን የኢትዮጵያ መንግሥት ሲረከብ የደቡብ ኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች የማይናቅ ማኅበራዊ ኃይል ሆነው ብቅ አሉ። ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በራሳቸው የሰውና የሐብት

ጥሪት አቅም ወንጌልን እየሰበኩ ለዘመናት ያልተደፈሩ ጥቅጥቅ ጫካዎችን ሁሉ መንጥረው የወንጌሉን ቃል ዘሩ። በ1931 ዓ.ም. ሦስት ብቻ የነበሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በ1935 ዓ.ም. ወደ 150 እንዲሁም በ1937 ዓ.ም. ደግሞ ወደ 250 ከፍ አሉ። የምዕመናን ቁጥርም 25,000 ያህል ደረሰ።

በእነዚህ አምስት ዓመታት የነበረው የቤተ ክርስቲያን እድገት ምን ያህል ፈጣንና መለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር እንዳለበት እንገነዘባለን። ከዚያ በኋላ ባሉት ሃያ ዓመታት ግን በየዓመቱ በአማካኝ 9.5% የቤተ ክርስቲያን እድገት ነበር የተመዘገበው። ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ አነስተኛ እድገት ያሳየችው 1957 እስከ 1965 ባለው ጊዜ ሲሆን ያም 6.66% ብቻ ነበር።[16]

*ዝርዝሩን ከሠንጠረዡ ያገናዝቡ*

| ዘመን(እ. ኤ. አ) | የቤተ ክርስቲያናት ብዛት | የዕድገት ዘመን | ዓመታዊ እድገት መጠን |
|---|---|---|---|
| 1938 | 3 | 1939–1942 | 36.75% |
| 1942 | 150 | 1943–1945 | 22.00 % |
| 1945 | 250 | 1946–1950 | 9.52% |
| 1950 | 369 | 1951–1955 | 9.16% |
| 1955 | 538 | 1956–1960 | 9.73% |
| 1960 | 800 | 1961–1965 | 9.60% |
| 1965 | 1184 | 1966–1970 | 7.08% |
| 1970 | 1603 | 1971–1974 | 6.66% |
| 1974 | 2030 | 1975 | 13.30% |
| 1975 | 2300 | 1976 | 8.69% |
| 1976 | 2500 | 1977 | 8.00% |
| 1977 | 2700 | | |

[16] . Brant ,Howard. Church and Mission under fire in Ethiopia, 1974-1977. unpublished p. 7

ይህን ለልጆቻችሁ ንገሩ፣ ልጆቻችሁም ለልጆቻቸው፣
ልጆቻቸውም ለኋለኛው ትውልድ ይንገሩ። 
ኢዩ. 1፥3





# ምዕራፍ አንድ

## 2. የሽግግር ወቅት 1934–1939

ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. ጣሊያኖች አዲስ አበባን የተቆጣጠሩበትን 5ኛ ዓመት በዓል ሊያከብሩ በሚገባቸው እለት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ገቡ። በአገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከአምስቱ ዓመት ጦርነት የአስተሳሰብ ቅሪት ጋር የተያያዘ አዲስ የአስተዳደር ዘይቤ ፈር ተቀደደ። አርበኛና፥ ባንዳ፥ የውስጥ አርበኛና፥ ፊርማቶሪ . . . ወዘተ እየተሰኘ ለግለሰብ ሆነ ለተቋም የሚከበርበት ወይም የሚዋረድበት፤ ፊት የሚያገኝበት ወይም ፊት የሚነሳበት ማኅበራዊ ሚዛን ሰፈነ። ሚዛኑ ሚስዮን ጠቀስ የሆኑትን ቤተ ክርስቲያናት (ተቋማት) ብቻ ሳይሆን ነባር ቤተ እምነቶችንም ቢሆን ከጥያቄ ውስጥ አስገብቶ ነበር።[1] እርግጥ ነው በወረራ የመጀመሪያ ዓመታት አማራና ኦርቶዶክስ የፋሽስቶች ዋና የጥቃት ዒላማ ነበሩ። ከዚህም የተነሣ ለፋሽስት መንግሥት እውቅና ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ሚካኤልን ጣሊያን በጭካኔ ገድሎአቸዋል። ሁለቱ አቡኖች ወደ ሞት ሲነዱ ( በተለይም አቡነ ጴጥሮስ) ጣሊያኖችን ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ምድሪቱም እንዳትቀበላቸው ያደረጉት ግዝትና ሕዝቡም ለእንዲያ ያለ ግዝት የሰጠው ምላሽ የአርበኝነቱን ተጋድሎ ስለአፋፋመው በግዛት ዘመናቸው አጋማሽ የጣሊያን ሹማምንት በኦርቶዶክሳውያን ፊት መለሳለስ ጀምረው እንደ ነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።[2]

ጣሊያኖች አዲስ አበባን በተቆጣጠሩበት ዋዜማ እና ሰሞን አስር ያህል የሚስዮን ድርጅቶች በሥራ ላይ ነበሩ። እነርሱም የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን፥ የስዊድን የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች ሚስዮን፥

---

1 
2 ·ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ቅጽ አንድ፥ 1965 ዓ.ም. ገጽ 54
·መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያና መዝገቡ ምትኬ ቢልልኝ፥ (ትርጉም),1986 ገጽ 173፥ 232

የተባበረች የአሜሪካ ፕሬስቢቴሪያዊት ሚስዮን፥ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ሚስዮን፥ የሱዳን ኢንቲሪየር ሚስዮን፥( ኤስ. አይ. ኤም) የጀርመን ሄርማንስበርግ ሚስዮን፥ የፊላሻ ሚስዮን፥ ሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅብር፥ የወንጌል ስርጭት ማኅበር ( Society for the propagation of the Gospel ) የሚሰኙ የሚስዮን ድርጅቶችና ማኅበሮች ናቸው።

ሁሉም የሚስዮን ድርጅቶችና ማኅበሮች ምን ያህል የተከናወነላቸው ስለመሆናቸው ደፍሮ ለመናገር በቂ ጥናት ይጠይቃል። የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮንና የአሜሪካ ፕሬስቢቴሪያዊት ሚስዮን እንዲሁም የሱዳን ኢንቲሪየር ሚስዮንን የመሳሰሉት ግን በርካታ የትምህርትና የጤና ተቋሞችን ከፍተው በጊዜው ከነበረው የመንግሥት አቅም አንጻር ሲመዘን ቀላል ያልሆነ አገልግሎት አበርክተዋል። ሁሉም ከወረራው በፊት የነበሩት የሚስዮን ድርጅቶች ግን በቆይታቸው ወቅት አንድም የአገርኛ ቤተ ክርስቲያን ምስረታ ባለማደላደላቸው በዚህ ደካማ ጎናቸው ይመሳሰላሉ።

ከወረራው በኋላ ጣሊያኖች በኤርትራና በሌሎችም ቅኝ ግዛቶቻቸው እንዳደረጉት ሚስዮናውያኑን እንዲወጡ ሲያስገድዱ በኦሮሞች መካከል ሲሠራ የቆየውን የጀርመን ሄርማንስ በርግ የተባለውን የሚስዮን ድርጅት ብቻ በበጎ ተመለከቱት። ይህ የሆነው ጀርመንና ጣሊያን ከነበራቸው የጊዜው ወዳጅነት የተነሣ ነበር። ይህ የሚስዮን ድርጅት ከነጻነት በኋላ በተራ ዕጣ ፈንታው በቅድሚያ ከአገር እንዲወጣ የተደረገ ድርጅት ነው። ከዚህ ሌላ አሜሪካ ፀረ ፋሽስትና ናዚ አቋሟን ገልጣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ በይፋ መግባቷ ገና ያልታወቀበት ወቅት ስለነበር አሜሪካውያኑ የሚስዮን አባላት፥ እንደ እንግሊዛውያኑ እና እንደ ስዊዲናውያኑ መዋከብ ባይደርስባቸውም ኋላ ላይ ግን ተገፍተው መውጣቱ አልቀረላቸውም ነበር።

የኤስ. አይ. ኤም ሚስዮናውያን ተጠቃለው ከአገር ከወጡበት ከነሐሴ ወር 1929 ዓ.ም. ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ምንም ሳይሰሙ ዓመታትን አስቆጠሩ።

የውጭው ዓለም ስለኢትዮጵያውያን የወንጌል አማኞች ምንም መረጃ ያላገኘው በጣሊያን ወረራ ዘመን ወደ አገሪቱ የሚገቡ ወይም የሚወጡ ጽሑፎች ሁሉ በላቲን ቋንቋ ካልተጻፉ በስተቀር እንዳይተላለፉ የሚያግድ ደንብ ወጥቶ ስለነበር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የወንጌል አማኞች ደግሞ በላቲን ቋንቋ መጻፍም ሆነ ማንበብ ስለማይችሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[3]

የነጻነቱን ጦርነት የራሳቸውን የምሥራቅ አፍሪቃ ጥቅም ለማስከበር ሲሉ ከአርበኞች ጎን ሆነው የተዋጉት እንግሊዞች ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አዲስ አበባ ሲገቡ በሻለቃነት ማእረግ የአንድ የጦር ሜዳ ተመላሾች ማገገሚያ ማእከል አዛዥ ሆነው የተመደቡትና ከወረራው በፊት የኤስ.አይ.ኤም ሚስዮን አባል በመሆን በወላይታ ሲያገለግሉ የነበሩት ሚ/ር ሎውሪ ዳቪሰን መሆናቸው በደቡብ ባሉ ክርስቲያኖች ዘንድ ከታወ ቀበት ጊዜ አንሥቶ ግን የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ድልድይ ተበጀ።

የጣሊያን ወረራና የአርበኝነቱ ተጋድሎ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነትን አዳብሮ ስለነበር በዚህ ጦርነት ላይ 30,000[4] ያህል የከምባታና የአካባቢው ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ፋሽስቶችን ተዋግተው ስለነበር ምናልባት በእነርሱ በኩል ሳይሆን አይቀርም የዳቪሰን ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ዜና ለከንባታና ሃዲያ መሪዎች የደረሰው።

ሚስዮናውያኑ ስለ ብላቴናዋ ቤተ ክርስቲያን ለማወቅ ያላቸው ጉጉት ከፍተኛ የነበረውን ያህል የአገሬው ተወላጆችም የወንጌልን ብርሃን ስላበሩላቸው ስለ እነዚያ የባህር ማዶ አገልጋዮች ፍጻሜ የማወቅ ታላቅ ናፍቆት ነበራቸው። ስለዚህም አቶ ሽጉጤ ዳዳና አቶ ሰብሮ ወሰሮ ከከምባታና ሃዲያ በመነሣት የአንድ ሳምንት የእግር ጉዞ ተጉዘው በህዳር ወር 1934 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሚ/ር ዳቪሰንን አገኙ። ዳቪሰን ደግሞ

3 . Cottrell. F. Petter. Born At midnight. 1973 p 101
4 . Grenstedt. Staffan. Ambaricho. . . 1995 p

ከሁለቱ የወንጌል አማኞች የሰሙትን አስደናቂ የወንጌል ሥራ እና የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ዜና አጠናቅረው ባህር ማዶ አሻገሩት። የወንጌል ቤተሰቦች የሆኑት ሁሉ የምሥራቹን በመገረምና በጥርጥርም ጭምር ተቀበሉት። ሚስዮናውያን ከአገር ከወጡ በኋላ ተደጋግሞ ስሟ የማይነሳው የሲዳማ ቤተ ክርስቲያንም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰችው በዚሁ በዳቪሰን ሪፖርት ነበር።

> *አስደናቂ ዜና መጥቶልኛል፥ በአሁኑ ጊዜ ( በከምባታና ሃዲያ) ከሰባ በላይ ማኅበረ ምዕመናን መደበኛ የአምልኮ መርሐ ግብር ያካሂዳሉ። በሲዳማ አቶ ገነሜ . . .ታማኝ የመንጋው መጋቢ መሆኑን አስመስክሯል። የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪ አቶ ብሩ እጅግ የተንሰራፋ ሥራ ፈጽሟል ይላል ሪፖርቱ።*[5]

ከዚህም በተጨማሪ ሎውሪ ዳቪሰን ለባለቤታቸው በጻፉት ደብዳቤ ስለ እነ አቶ ሽጉጤና አቶ ሰብሮ ሲያብራሩ፡—

> በዚያ ሥፍራ በወላይታ የሚካሄደውን የእግዚአብሔርን ሥራ(ቤተ ክርስቲያናትን) ተዘዋውሮ ለመጎብኘት 15 ቀን እንደወሰደባቸው ነገሩኝ ። . . . አንዳንዶቹ ቤተ ክርስቲያናት *ከአንድ መቶ በላይ ሰዎችን ይይዛሉ፤ በምሽትና በሌሊት ለሚካሄዱ ስብሰባዎች ከአምስት እስከ ሰባት ፋኖሶች ወይም ኩራዞች መጠቀም ያስፈልጋል። ከሩቅና አመፀኛ ከሚባሉት ጎሳዎች ሳይቀር ሰዎች መጥተው ከእኛ ጋር ያመልካሉ፤ በማለት ዘግበዋል።*[6]

እነ አቶ ሽጉጤ ስለ ከንባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በወላይታ ስላለችውም ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት ያብራሩት እንደሚከተለው ነበር።

> *ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ አማኝ እንኳን ለማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ከሆነበት ከማረቆ አካባቢና ( በጊዜው ማረቆና ወላይታ የጎሣ ግጭት ያደርጉ ነበር) ከጎፋም ዳርቻ ጭምር ከወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪ ከአቶ ብሩ ትምህርት ለመቅሰም ብዙ ሰዎች ይመጣሉ፤ አስርና አስራ አምስት ቀናት ያህልም ቆይተው ልባቸው ለጌታ ሥራ ተቀጣጥሎ ይመለሱ ነበር።*[7]

---

[5] . Cottrel . 1973 p. 101
[6] . Balisky. Wolaita Evangelists. 1992 p. 188
[7] . Ibid

ይህ ከሆነ ከስምንት ወር በኋላ አቶ ብሩ ዱባለ እና የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሆኑ ጥቂት ሰዎች ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሚ/ር ዳቪስንን በግምባር አግኝተው እግዚአብሔር በዚያች ምድር ያደረገውን ተአምራታዊ ሥራ ተረኩላቸው። የሰሙት ሁሉ ከአእምሮ በላይ የሆነባቸው የቀድሞው ሚስዮናዊ፡-

> *. . . ብሩ የነገረኝን ሁሉ ልጽፍላችሁ አልሞከረውም፤ ከእርሱ ጋር አብረው ሌሎች ሰስት የወላይታ ክርስቲያኖችም ነበሩ፤. . . እርሱ የነገረኝን ሁሉ ደግመው ተረኩልኝ። እንዲያውም አዳዲስ ነገሮችን ጨምረው፤ ብሩ አስደናቂ ሥራ እንዳደረገ ጥርጥር የለውም። አዲስ ክርስቲያን ለአንድ ዓመት ያህል መንፈሳዊ ነገሮችን ካላጠና በስተቀር አይጠመቅም፥ እንዲያም ሆኖ በአንድ ቀን አምስት መቶ ሰው ያጠመቀበት ቀን ነበር።* [8]

የእነዚህና የሌሎችም ሪፖርቶች መሰማት በርካታ ሚስዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ ዳግም እንዲመጡ ልባቸውን አነሳስቷል። ከጣሊያን ሽንፈት

ከሁለት ዓመት በኋላ በሐምሌ ወር 1935 በሶዶ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ ፈቃድ ያገኙት የኤስ. አይ. ኤም. ጠቅላይ ቢሮ ድሬክተር ዶክተር ፕሌይ ፌር « Trial and triumphs in Ethiopia » በተሰኘው መጽሐፋቸው የዘገቡትን በመጥቀስ አንድ ጸሐፊ እንደ ተረኩት፡-

> *ይህ ዝም ብሎ የወጣቶች ንቅናቄ አይደለም፥ ሁሉንም የእድሜ ክልል ያጣቀሰ ነውና . . . ሦስት መቶ ያህል ምእመናን ባሉበት ጉባኤ ውስጥ ከሃያ በላይ ሽበታም አዛውንቶች ቆጥረናል፤ ምናልባት ሁሉም አያቶች ሳይሆኑ አይቀሩም። አብዛኛው ተሳታፊ ዕድሜ ግን ከሃያ አምስት ዓመት በላይ የሚሆናቸው ወንዶችና ሴቶች ናቸው፤ ብለዋል።*[9]

ዶ/ር ፕሌይ ፌር ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ሰባት ዓመት በአገር ሰዎች አስተባባሪነት ራሷን በራሷ ከመራች በኋላ ነበር። ከሰባቱ ዓመታት ውስጥ አምስቱ የወረራ ዓመታት የመከራና የስደት ዓመታት ናቸው። አርበኞችና እንግሊዞች ወላይታ ሶዶ በድል አድራጊነት ሲገቡ ግን አሳዳጆቻቸው ጣሊያኖችና ባንዳዎች ተራቸውን በምርኮኝነት ታሠሩ። የዓይን ምስክሮችን ዋቢ በማድረግ አንድ ጸሐፊ

---

8 . Ibid
9 . Ibid. p 190

እንደዘገቡት በዚያን ወቅቱ ( ሜይ 22 ቀን 1941) አራት ሺህ ያህል የጣሊያን ወታደሮች በምርኮኛነት ተይዘው ነበር።[10]

ገዢዎቹ ወደ እስር ሲገቡ ስደተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ ወደ አደባባይ ወጣች። ይህንን ነጻነት መለማመድ በጀመረች ከጥቂት ዓመታት ውስጥ ነበር ፕሌይፌር ሰዶን የጎበኙትና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ብዛት 300 ያህል ይሆናል የአማኙም ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ሲሦ ውን ያህላል ብለው የገመቱት።[11]



ጥቂት የአፎይታ ዓመታት 1934–1938

በወላይታ በመቶ የሚቆጠሩትና በአራቱም ማዕዘናት የተሰራጩት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ኃላፊነት በአቶ ብሩ ዱባለ ዙሪያ መከማቸቱ ያሳሰባቸው ዶ/ር ፕሌይፌር አጥቢያዎች እንደየቅርበታቸው ተደራጅተው በአንድ መሪ ሽማግሌ እየተወከሉ አስራ

[10] . Thompson, Robert N. Liberation, The first to be free. 1987 p. 178
[11] . Balisky. 1997 p. 190

አምስት ያህል ተጠሪዎች የጠቅላላውን ማኅበር እንቅስቃሴ ከአቶ ብሩ ጋር ሆነው እንዲያስተባብሩ ግፊት ያደረጉትም በዚህ ወቅት ነበር።

ይህ የኃላፊነት በጥቂት ታዋቂ ሰዎች ዙሪያ መሰባሰብ በወላይታ ብቻ ሳይሆን በከምባታና ሃዲያም የተከሰተ ነበር። ከጣሊያን ወረራ ጀምሮ ለተከታታዩ ሰላሳ አምስት ዓመታት ያህል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው ስቴፈን ግሬንስድት "ሦስቱ ትልቆች" ወይም ሦስቱ አእማድ ( The big three ) ብሎ በሰየማቸው አባጎሌ ኑነሞ፥ አቶ ሽጉጤ ዳዳ እና በአቶ ሰብሮ ወሰሮ ስም ዙሪያ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሲሽከረከር መኖሩ እርግጥ ነው።[12] ምንም እንኳን የታዩ ጥቃቅን ችግሮች ቢኖሩም፡- ብርቱ ሰው ለብርቱ ቀን ይጠበቃል እንዲሉ ባለፉት ከፉ ዓመታት ብርቱ ሰው ያላሳጣን እግዚአብሔር ይመስገን።

የተነሣንበትን የወላይታን ሁኔታ ያየን እንደሆነ ግን ለየት ያሉና ውስብስብ ጉዳዮች ይኖሩታል። ሁሉንም ለመጠቃቀስ የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዓላማ አይደለም፤ ጥቂቱን መነሻ ደግሞ በቅጽ አንድ ከአቶ ብሩ የሕይወት ታሪክ ጋር አስተሳስረን ነካክተነዋል።[13]

በሌላ በኩል ግን በመቶ የሚቆጠሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን በአስር ሺህዎች የሚገመቱ ምእመናንን ስህተት አልባ በሆነ መንገድ ፍጹም ያለነቀፋ ለመምራት ሰው ከመሆን በላይ ልዩ ፍጥረት መሆንን የሚጠይቅ እንደሆነ እነዳቪሰን የዘነጉት ይመስላል። ባይሆን ኖሮ አገርኛውን የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ዘይቤ እንደሚበጅ አድርገው ያቀኑታል እንጂ አቃቂር ባላበዙበትና ለውስጣዊ "የዋነኛነት" ሽሚያ ሊያጋልጡት ባልተገባ ነበር [14]፤ የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አልጠፉም።

---

[12] . ወንድዬ ዓሊ፥ በመከራ ውስጥ ያበበች ቤ.ክ 1990 ገጽ 237
[13] . ዝኒ ከማሁ ገጽ 208-215
[14] . Cottrell . 1973 p.105-106

# የቤተ ክርስቲያን መደራጀት

ያም ሆነ ይህ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ከ1934 እስከ 1938 ዓ.ም. ድረስ አገልግሎቷን ይፋ ባወጣችው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኀበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በወላይታ ከአቶ ብሩ ሌላ አቶ ዋንዳሮ፥ አቶ ቶሮ አቶ ደያሳ ዳርጌ፥ አቶ ጎዳና፥ ዳና ገደቦ፥ ዳና መጃ መደሮ እና የእነሱ ዘመነኞች እንደማኀበር አለቃ ብቅ ብለው መታየት ጀምረው ነበር።

በከምባታና ሃዲያ ደግሞ " ከሦስቱ . . . " ሌላ አቶ ረጠቦ አመሌ፥ አቶ አበበ ቡሽሮ፥ አቶ ሞለሮ መሌቦ፥ አቶ ሀፍሶ ቲሮሮ፥ አቶ ዶቼ ደንታሞ እና የእነሱ ዘመነኞች ከዋናዎቹ ተርታ ስማቸው አብሮ ይጠራ ነበር።

ከላይ እንደተጠቀሰው በወላይታ በዶ/ር ፕሌይፌር አነሳሽነት ሦስት ደረጃ ያለው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ተዘረጋ። ጣሊያኖች ያፈረሷቸውን ከ60 የማያንሱ ጸሎት ቤቶችን እንደገና ከመሥራት ጎን ለጎን የወንጌል እሳት ከወላይታ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ በአስገራሚ ፍጥነት መቀጣጠል የጀመረውም በዚሁ በአጭር የሽግግርና የነጻነት ወቅት ላይ ነበር።

መዋቅሩ ቀበሌ፥ ወረዳ፥ አውራጃ አቀፍ ሆኖ አጥቢያዎች ተሰባስበው ክፍለ ማኀበርን፤ ክፍለ ማኀበራት ተሰባስበው እድርን፥ የእድሮች ኅብረት ደግሞ አውራጃን ወይንም ወላይታዎች ለረዥም ጊዜ የሚጠቀሱበትን "ጠረጴዛ " ወይንም "ሆስፑን ዳና" የሚባለውን ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ይፈጥራል። በከምባታና ሃዲያ የመዋቅሩ ስያሜ አጥቢያ፥ ክበብ፥ ክፍለ ማኀበር አውራጃ ወይም ወንጌላዊት ይባላል።

በወላይታ ከክፍለማኀበራት ተወክለው በወር አንድ ጊዜ ጉባኤ የሚሰየሙት የቦርድ አባላት ከጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ከሚመክሩበትና ከሚያስተላልፉት ውሳኔ የተነሣ ይመስላል "ጠረጴዛ" የሚለውን መጠሪያ ያገኘው። "የጠረጴዛ" ውሳኔ ለወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እስትንፋስ ነው፤ አቅጣጫዋ የሚቀየስበት፥ መስመር የለቀቀው ፈር

የሚይዝበት፥ የሥነ ስርዓት ጉድለቶች የሚታረሙበት፥ ግለሰቦች የሚዳኙበት፥ የወንጌል ጥሪ ጉዞ ( ስምሪት) ይሁንታ የሚጠበቅበት ስለሆነ ታላቅ ከበሬታ ይሰጠዋል። በአብዮቱ ዋዜማ ላይ በ16 ክፍለ ማኅበራት የተደራጁትን 700 ያህል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ስናስብ ጠረጴዛው ምን ያህል ከባድ ኃላፊነት እንዳለበት እንገነዘባለን

በከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመደራጀት ጥያቄ የተነሳው ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ስለ ነበር ሂደቱ የተጠናቀቀው ያለ ብዙ እንግልት እና የጎላ መሽካከር ሳይኖር ነበር። በ1937 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች በኢልጊራ ሰባት በጥንግራ ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው የወንጌልን ሥራ መስፋት፥ የቦታውን እርቀት፥ የምእመናንን መብዛት በጥልቀት ተወያይተው አጥቢያዎችን በክፍለ ማኅበራት ደረጃ እንደ እየቅርበቱ የሚመድብ አራት አባላት ያሉበት ኮሚቴ ሰየሙ። [15]

የኮሚቴው አባላት አቶ አበበ ቡሽሮ ፥ አቶ ሞሎሮ መሌቦ፥ አቶ ሀፌሶ ቴሮሮ እና አቶ ዶቼ ደንታሞ ሲሆኑ አውራጃውን ለሰባት ቀጣናዎች ሸንሽነው ከ30 እስከ 40 አጥቢያዎችን ያቀፈ ሰባት ክፍለ ማኅበራትን አደራጁ። ማኅበሩንም "ሰባት" ሲሉ ሰየሙት። ለመጀመሪያ ጊዜ የተደራጁት (ሰባቶች) ማኅበራትም፦

| | |
|---|---|
| ሊሙ ሰባት | አሺሬ ሰባት |
| ድኒቃ ሰባት | ኢልግራ ሰባት |
| ዳንሳአ ሰባት | አምቡርሲ ሰባት ናቸው |
| ቃጫ ሰባት | |

ክፍለ ማኅበራቱ ለምን "ሰባት" ተብለው እንደተሰየሙ በውል የሚያውቅ ሰው የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አጠያይቆ ነበር፦

---

[15] ታምሩ አበሞ፥ ቤተ ክርስቲያንና የልማት እንቅስቃሴ 1976ዓ.ም. ገጽ 31

ታሪክ ጸሐፊው አቶ ታምሩ አበሞ "ሰባት" በከምባታና ሃዲያ ባህል "እንደ ሙሉ" "እድለኛ" ቁጥር አድርጎ ማሰብ የተለመደ ነው፥ ነገር ግን አባቶች ለማኅበራቱ ይህንን ስያሜ ሲያወጡ ባህሉን ተመርኩዘው አይደለም የእግዚአብሔር መንፈስ መርቷቸው እንጂ ይላሉ።[16]

በሌላ በኩል ደግሞ ወንጌል ከተሰበከላቸው በኋላ አምነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የጀመሩት ሰባት ሰዎች ስለነበሩ ሌላውም እያመነ የአማኒያን ቁጥር ሲበራከት መጽሐፍ ቅዱስን ሰባት–ሰባት ሆኖ ማጥናት ተለመደ፥ ቀጥሎም የሕዝብ ውርስ ሆነ፥ የሚሉ ሰዎችም ያጋጥማሉ።

ከቀዳሚ መሪዎች አንዱ የሆኑት አባዶጊሶ (ሰብሮ ወሰሮ) ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን መላምቶች ሳይሽሩ ሰባት የመደራጀታችን ምስጢር በራእይ መጽሐፍ ውስጥ " ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት" የሚለውን በማንበባችንና ስለሰባት ካለን የቀድሞ ግንዛቤ ጋር ስለገጠመልን እንጂ የራእይ መጽሐፍ ትርጓሜ ዘልቆ ገብቶን አይደለም ይላሉ። [17]

በከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን "ሰባት" የኅብረቱ ስያሜ ቢሆንም በአንድ ሰባት ውስጥ የሚሰባሰቡት አጥቢያዎች ብዛት ከሰባት በላይ ሰላሳም እስከ አርባም ሊሆን ይችላል። በአንድ "ሰባት" (ማኅበር) ውስጥ ያሉት አጥቢያዎች ተበራክተው መንጋውን በቅርብ ለመከታተል ሲያዳግት ከሰባቱ ውስጥ ሌላ አዲስ ሰባት ተደራጅቶ እንዲወጣ ይደረጋል። ከዚህም የተነሣ በአብዮቱ መባቻ ላይ በከምባታና ሃዲያ ወንጌላዊት ከ23 ያላነሱ ሰባቶችና ከ600 በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተደራጅተው እንደ ነበር ታውቋል።

በአውራጃ ደረጃ ያለውንና የአውራጃዋን ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሚፈጥረው የየሰባቱ ( የማኅበሮቹ ) ተወካዮች በርድ ነው። በአውራጃ ደረጃ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን "ወንጌላዊት" ይሏታል።

---

16 . ዝኒ ከማሁ ገጽ 32
17 . ሰብሮ ወሰሮ ( አባዶጊሶ ), ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥
ነሐሴ 1988 ዓ.ም ላምቡዳ ሃዲያ።

የወንጌላዊቱ ጉባኤ የሥራ ድርሻ ከወላይታው ጠረጴዛ ጋር ተመሳሳይነትና በብዙ ጉዳዮችም አንድነት አለው። ወንጌላዊት የሚለውን ስያሜ በጣሊያን ወረራ ወቅት እነ አቶ ሽጉጤ ዳዳ እና አቶ ሰብሮ ወሰሮ ከስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን መሪዎች ከእነ አቶ አማኑኤል ገ/ሥላሴና ከነቄስ ባድማ ያለው ጋር ከነበራቸው ቅርርብ የቀዱት (የወሰዱት) ስያሜ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል።

ያም ሆነ ይህ በሁለቱ አውራጃዎች ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብላ መደራጀቷ ከአቻ ማኅበሮችና ከብሔራዊ የቤተ ክርስቲያን ተቋሞች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እርስ በርስ ለመረዳዳትም መንገድ ከፍቶላቸው ነበር። ዳሩ ግን አስቀድሞም ከእውቀት ማነስ፥ ኋላም በሚስዮናውያን ጣልቃ ገብነት ሁሉ ነገር እንደታሰበው አልሰመረም። በሚቀጥሉት ገጾች በዝርዝር እንመለከተዋለን።

# 3. ቀደምት ቤተ ክርስቲያናትና

## የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ

የወንጌል አማኞች አስቀድሞም በነባር ቤተ እምነቶችና በመኳንንቱ ኋላም በጣሊያኖች እጅ መራራ የስደት ፅዋን እንዲቀምሱ መገደዳቸው እርስ በርስ እንዲተጋገዙ፥ እንዲመካከሩና የወንጌል ስርጭት ስልት እንዲነድፉ አነሳሳቸው።

እንደዛሬው ዘመን የወንጌል አማኞች በአገሪቱ ማዕዘናት እንደልብ በማይገኙበት ወቅት በከምባታና ሃዲያ እና በወላይታ በብዛት ከተተከሉትና እንዲሁም ከሲዳማ ቤተ ክርስቲያናት ሌላ በማእከላዊ የአገሪቱ ክፍል ውል ያለው የወንጌል ሥራ የሚያከናወኑ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። ከሁሉም ቀደም ብለው የገቡት ሉተራውያን

እንኳን እስከ 1961( እ. ኤ. አ) ድረስ በመላ አገሪቱ የነበራቸው አጥቢያዎች 39 ብቻ መሆናቸውን ያስታውሷል።[18]

በድኅረ ወረራ ማግሥት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሁለት ብቻ ሲሆኑ፥ እነሱም በኋላ ላይ "የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያ" የተሰኘው የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን አንዱ ሲሆን ሁለተኛው የስዊድን የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን ነው። ከነዚህ ተርታ ባይደመርም የሰባተኛ ቀን አድቬንትስት ሚስዮን ሦስተኛው ነው።

የመጨረሻዎቹ ሁለቱም ቢሆኑ የራሳቸው የማምለኪያ ቦታ ሠርተው በቅጡ የተደራጁና በጊዜው የነበረውን ማዕበል ፊት ለፊት ተጋፍጠው ለመቋቋም የበቁም አልነበሩም።

ስቴፈን ግረንስቴድ እንደሚለው ጣሊያኖች ከአዲስ አበባ በእስር አግዘዋቸው በሶማሊያ ለጥቂት ዓመታት በግዞት የቆዩት የአቶ አማኑኤል ገብረ ስላሴ በኋላ ዶ/ር መፈታትና ተመልሰው አዲስ አበባ መምጣት፥ መጥተውም በሰኔ ወር 1933 ዓ.ም. የአዲስ አበባን ማኅበረ ምዕመናንን እንደገና ማቋቋማቸው ከሩቅና ከቅርብ አዲስ አበባን ለሚጎበኙ የወንጌል አማኞች መሰባሰቢያ ጥላ እንዲያገኙ ረድተቻቸዋል።[19] ይህም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጥንስስ ሆነ።

ዋና ዋናዎቹ የሚስዮን ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው እስኪገቡ ድረስ በወንጌል አማኞቹ መካከል የነበረው ግንኙነት ከጣልቃ ገብነት የነጻ ነበር። ከላይ የተጠቀሰው ደራሲ አቶ አማኑኤል ገብረ ሥላሴን ጠቅሶ እንደዘገበው "በዚያን ዘመን በወንጌላውያን ክርስቲያኖች መካከል ምንም ልዩነት አልነበረም፤ ሚስዮናውያን እንደገና ከመግባታቸው በፊት እኛ እና የኤስ. አይ. ኤም ክርስቲያኖች አንድ ነበርን" በማለት የግንኙነታቸውን ጥንካሬ ተናግረው እንደነበር ታውቋል። በአፍላው

[18] Cottrel. 1973 p. 136
[19] . Staffan. Grenstedt 1995 p. 60

የጣሊያን ስደት ወቅት አማኞች እርስ በርስ ለመመካከር ከተጠቀሙበት መንገድ በአዲስ አበባ ዋና ዋና ጎዳናዎች ዳርቻ እንደቆሎ ነጋዴና ገዢ በመምሰል ተቀራርበ መነጋገር አንዱ ዘዴአቸው እንደነበር አንጋፋ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መስክረዋል ።[20]

አስተዋይ መሪዎች የቤተ እምነትንና የእኔነት ጥያቄን ወደ ጎን ትተው እርስ በርስ ኅብረትን እንዲፈጥሩ አስከፊው ስደት የከፈተላቸውን በር ወደተሻለ ግብ እንዲደርስ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረውበታል። ጥረቱ ተጠናክሮ ከነጻነት በኋላ ይበልጡን ይፋ በመውጣት እንደ ማንኛውም ነፃ አገር ብሔራዊ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የሚያበቃቸውን መሠረት በመጣል “ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ” የተሰኘ አካል ለመፍጠር ሁኔታዎችን አመቻቹ።

“ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ” በመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፥ በአምልኮ ሥርዓት፥ በውስጥ አስተዳደርና በመሳሰሉት የአስተዳደር ፈሊጦች ያልተከፋፈለች፥ እንዲሁም የውጭ ሚስዮናውያን የማይሰለጥኑባት ብሔራዊና አንድ ወጥ መልክ ያላት ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም በታህሳስ ወር 1937. ዓ.ም. ስብሰባ ሲጠራ አንድም የውጭ ሚስዮናዊ እንዲካፈል አልተጋበዘም ነበር። በአንጻሩ ግን በየትኛውም ወንጌላዊት የሚስዮን አገልግሎት በኩል ወንጌልን የተቀበሉና በመላ አገሪቱ ያሉት ማኅበረ ምእመናን በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ጥሪ ተደረገላቸው። እነ አባ ጎሌም ጥሪው እንደደረሳቸው ተረጋግጧል። የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጉባኤዎች በ1937 ዓ.ም. በምዕራብ ኢትዮጵያ ወለጋ ክፍለ ሐገር በነቀምት ስለተካሄዱ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች አልተሳተፉም። ያለመሳተፋቸው ምክንያት ከስብሰባው ቦታ ርቀት የተነሳ እና የገንዘብ አቅም ማነስ እንደሆነ ይገመታል። እንደ አውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ከ1947 ጀምሮ እስከ 1963 በተካሄዱት

20 . አባጎሌ ኑነሞ፥ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥
ነሐሴ 1988 ላምቡዳ ሃዲያ።

አምስት ስብሰባዎች ላይ ግን የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ተሳታፊ ነበሩ።

በጥቂቱ ዘርዘር አድርገን ብንመለከተው ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት አብዛኛውን ጊዜ "በሦስቱ" እየተወከለች የከምባታና ሃዲያ ወንጌላዊት ሙሉ በሙሉ ስትካፈል የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ግን አንድ ጊዜ ብቻ በ1955 ( እ. ኤ. አ.) ለዚያውም በታዛቢ ደረጃ ተካፍላለች። የጋሞ ጨንቻ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በ1952 እና በ1955 ተወካዮቿ ልካ ተካፍላለች። ይህ እንግዲህ ጉባኤው በይፋ መሰባሰብ የጀመረበትን ወቅት ለማመልከት እንጂ በአመሠራረቱ ሂደት ላይ ግን ከ1934 አንስቶ አቶ ብሩና" ሦስቱ" አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ታውቋል።





*ሦስቱ ( THE BIG THREE)*

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ገና በመጀመሪያው የነቀምቴው ስብሰባ ላይ ጠንካራ የሆነ አገርኛ ስሜትን በማንጸባረቅ ተወካዮች ሁሉ አንድ ወጥ አሠራርን እንዲቀይሱ ጥሪ ያደረገ ጉባኤ ነበር። ሁለተኛው ከፊተኛው ይልቅ አንድ እርምጃ ተራምዶ ልትመሠረት

ያላት ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን " የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን" ተብላ እንድትጠራ ውሳኔ አስተላለፈ። በሦስተኛው ጉባኤ ደግሞ በተለያየ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ዳራ( Back ground ) የተቋቋሙት ቤተ ክርስቲያናትን ሊያስተሳስር የሚችል የሃይማኖት መግለጫ (የእምነት አንቀጽ) እንዲቀረጽ ውሳኔ አስተላለፈ። መግለጫውንም የሚቀርጽ ኮምሲዮን ሰየመ። የኮምሲዮኑ አባላት የሥነ መለኮት እውቀት የዘለቃቸው ያለመሆናቸው ኃላፊነታቸውን በጊዜው እንዳይወጡ ጫና ከሆነባቸው ችግሮች አንዱ ነው። ኮሚቴው የተጣለበትን አደራ ከመወጣቱ በፊት ግን በወረራው ምክንያት ከአገር ተባረው የነበሩት የሚስዮን ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ በገፍ መመለስ ጀመሩ። ከነባሮቹ የሚስዮን ድርጅቶች ሌላ የኖርዌጂያን ሉተራን ሚስዮን፥ የዴንማርክ ወንጌላዊት ሚስዮን፥ የአሜሪካን ሉተራን ሚስዮን በቅድሚያ፥ ቀጥሎም የተለያዩ የባፕቲስት ሚስዮኖች እንዲሁም መሠረተ ክርስቶስን ያበቀለው ሜኖናይት ሚስዮን፥ ጳንጠቆስጤውና የብርሃን ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን የተከለው የፍላደልፊያ ሚስዮን እንዲሁም ሌሎች የሚስዮን ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ ገቡ።

ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ዳግመኛ እንደተመለሱ ያገኟት ቤተ ክርስቲያን መዓዛ ሐበሻ ሐበሻ መሽተቱ በጣም አስገርሟቸው ነበር። ሆኖም ለአገርኛ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ የተደረገውን ጥረት በቅንነት የተመለከቱት ጥቂቶች ነበሩ።

እንዲያውም መጥተው በየክፍለ ሐገራቱ ከመሰማራታቸው በፊት ሚስዮናውያኑን ብቻ የሚያቅፍ ማኅበር አቋቁመው የአገሪቱን የቆዳ ስፋት በካርታ በመከለል የሥራ ቀጣና ተከፋፈሉ። ዳሩ ግን ምክራቸው ኢትዮጵያውያን የወንጌል ሰዎችም ሆነ በመከራ ውስጥ የተወለዱትን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ባለ ማሳተፉ በተጨማሪም የኢትዮጵያን መንግሥት የወደፊት ፖሊሲ ያገናዘበ ባለመሆኑ ውጤት አልባ ሆነ።

ሚስዮናውያኑ አገሪቱን በክልል ሸንሽነው አንዱ የሚስዮን ድርጅት በሌላው ድርጅት ቀጣና ወይም ክልል እንዳይገባ መልክዓ

ምድራዊ ድንበር አበጅተውለት መደላደላቸውን አንዳንድ ጸሐፊዎች ከአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች "Scrumple for Africa" በተሰኘውና አፍሪቃን ለመቀራመት በ1845 (እ.ኤ.አ) በበርሊን ተገናኝተው ካደረጉት ውሳኔ ጋር ያመሳስሉታል። [21]

ሚስዮናውያኑ ማኅበር መሥርተው ድንበር ተካልለው ለሥምሪት መነሳታቸው ሥራቸውን"አልጋ በአልጋ" አላደረገላቸውም፤ እንዲያውም አንዱ ሌላውን ከልሌን ጣሰ፥ ድንበሬን ደፈረ እያለ ለመክሰስ መነሻ ከማግኘቱና ለኅብረቱ የማያቋርጥ የንዝንዝ መድረክ ከመፍጠሩ ውጭ ፋይዳ ያለው አወንታዊ አሻራ አላመጣም። ይልቁንም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ኢትዮጵያውያን መነሻ እንዲሆናቸው በአቋቋሙት ጉባኤ ግብና ስኬት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አፍራሽ ጥላውን አጠላበት እንጂ። ሁሉም የሚስዮን ድርጅት በየሰበካውና በአቋቋማቸው ማኅበራዊ ግልጋሎት መስጫ ተቋማት ላይ የላኪ ቤተ ክርስቲያናቸውን ዶክትሪን በመጫን የአገሬውን የወንጌል አማኞች ብሔራዊ ኅብረት የሚፈታተን ግድግዳ ሠሩ።[22] በዲኖሚኔሽን ( ቤተ እምነት) የመከፋፈልን አባዜ በኢትዮጵያውያኑ አእምሮ ውስጥ እንደሸቀጥ አራገፉ።[23]

እያንዳንዱ ሚስዮን የገዛ ሰበካውን ፍሬዎች ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ሳይሆን ወደየራሱ ጎተራ አከማቸ። ኤስ. አይ. ኤም ስልቱን ለወጥ በማድረግ በምእመናኑ መካከል የሥነ ምግባር ጉዳዮች ( ethical issues ) ክርክር ጫረ።[24] አዳዲስና አክራሪ-መሰል የሚስዮን ድርጅቶች ብዛት በጨመረ መጠን የአንድነቱ ጥያቄ ለዛ አጣ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን በአንድ ወጥ የእምነት መግለጫ ወይንም እንደ አማራጭ ቀርቦ በነበረው

---

[21] . Bakke, Johnny. Christian ministry. . . 1986 p. 160
[22] . Soveras, olav. On Church - Mission Relations in Ethiopia 1944-1969. 1972 p. 76-79
[23] . Staffan. Grenstedt 1995 p. 66
[24] . Ibid p. 71

በፌዴሬሲዮን አወቃቀር የመሰባሰብ ምኞትን የሚያከስመ ተጨማሪ ታሪካዊ እውነቶች ተከሰቱ።

የመጀመሪያው እንደ አውሮፖውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ1947 የተመሠረተው የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሲዮን በዓለም ዙሪያ የሚገኙት የተለያዩ የሉተራን ሚስዮኖች በየሚሠማሩበት አገር እንቅስቃሴአቸውን እንዲያቀናጁ በ1951 (እ.ኤ.አ.) ውሳኔ ማስተላለፉና በኢትዮጵያም ውስጥ የነበሩት አምስት ሉተራውያን ሚስዮኖች ለብቻ መደራጀት መጀመራቸው ነበር።[25] ከሦስት ዓመት በኋላ ቅንጅቱ በብሔራዊ ደረጃ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ወደ መመሥረት አቅጣ አመራ። ከሌላ ሦስት ዓመት በኋላ በ1957 እ.ኤ.አ.“የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን” ለመመሥረት ቀዳሚ አነሳሽ የነበረችው “ መካነ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን” ወይም የአዲስ አበባ ወንጌላዊት ማኅበር የዓለም አቀፉ የሉተራውያን ፌዴሬሲዮን በአባልነት ተቀበላት። ይህች ማኅበር የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን ለማቋቋም የነበራትን የቀዳሚ አነሳሽነቷን ቀስ በቀስ አረገበች። በአንጻሩ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩትን ሁሉንም ሉተራውያን ቢቻላትም ሌሎቹንም የወንጌል አማኞች ሁሉ አስተባብራ ብሔራዊት ሉተራዊት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ብርቱ ጥረቷን ተያያዘች። በ1958 እ.ኤ.አ.(1951ዓ.ም.) የሉተራውያን ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች። የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ዋነኛ አዝማቾች የነበሩት እነ አቶ አማኑኤል ገብረ ሥላሴ፣ ቄስ ባድማ ያለው፤ ቀደም ሲልም እነ አቶ አማኑኤል አብርሃም ሉተራውያን ስለነበሩ ትኩረታቸውን ወደ ቤተ እምነታቸው ምሥረታና መዋቅር ቀረጻ እንዲያዛውሩ ጊዜው ግድ አላቸው። ከአምስት ዓመት በኋላም የመጀመሪያ ሕልማቸው ዳግም ላይነሣ ሟምቶ ቀረ።

---

[25] . Mekane Yesus Seminory. History of christianity in Ethiopia. 1992. p. 83

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን ባልጠበቀ አንድነት በፌደራሲዮን አቋም ለመመሥረት እንደ አማራጭ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም ተግባራዊ እንዳይሆን ከጎተቱት ምክንያቶች በ1943/44ዓ.ም. የተፈጠረው የከምባታና ሃዲያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል አንዱ ነበር የሚሉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተንታኞችም አሉ።[26]

የመከፋፈሉ ጥንስስ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ በይፋ የተገለጠው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በጥር ወር 1944 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ጉባኤ በተቀመጠበት ወቅት ነበር። በዚህ ወቅት የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ከቀደምት መሪዎች አንዱ ማኅበሩን ለመከፋፈል እንደተነሡ አጋልጠው ጉባኤው " ሃይ " እንዲልላቸው ወይንም ጉዳዩን አጥንቶ እንዲፈርድላቸው ጠየቁ።[27] ተወካዮቹ የኤስ.አይ.ኤም. ሚስዮንን አልፈው ገና ለገና ቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት ለሚፈጨረጨር ጉባኤ አቤቱታ ማቅረባቸው በጊዜው የጠንካራ አገርኛ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ምን ያህል አንገብጋቢ እንደነበር ይጠቁማል፤ የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ እንዲሉ።

ጉባኤው በበኩሉ በከምባታና ሃዲያ ወንጌላዊት ውስጥ የተነሣውን ችግር ለማርገብ የአዲስ አበባ ወንጌላዊት ማኅበርን ( ዛሬ የአዲስ አበባ መካነ የሱስ የሆነችውን) በአስተራቂነት ሰይሟት በወቅቱ ፕሬዝዳንቷ በአቶ አማኑኤል ገብረስላሴ መሪነት የተጣሉትን ሁለቱን ወገኖችና ኤስ.አይ.ኤምን በማነጋገር የእርቅ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ችሎ ነበር። የቀየሰው ስልት ግን ሰላምን ሊያወርድ አልቻለም።

ይልቁንም በእርቁ ሂደት ከመካነ ኢየሱሶች ጋር መግባባትን የፈጠረው ቡድን በአልታሰበ ሁኔታ በ1955 (እ.አ.ኤ) ቤተ ክርስቲያኒቱን ተቀላቅሎ ኋላ ላይ የከምባታ ሲኖዶስ የሚል ስያሜ የተሰጠውን ሲኖዶስ ለመፍጠር ቀንጆ መሸጋገሪያ ሆነ።

---

26 . Ibid p. 83
27 Staffan. Grenstedt. 1995 p. 69

ስለዚህም ጥልቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፥ ጥብቅ አስተዳደራዊ መዋቅር፥ የሌላት ቤተ ክርስቲያን የየዘመኑ ክፋት የሚያስነሳባትን ተግዳሮት መቋቋም እንደሚሳናት ተግባራዊ ትምህርት የቀሰሙት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ መሪዎች የተለያየ ዶክትሪን ያላቸው ሚስዮናውያን የተከሏቸውን የተበታተኑ ቤተ ክርስቲያናት መቋጫው ባልጠበቀ አንድነት ከማስተባበር ይልቅ እነሱም ሉተራውያን ናቸውና " የሉተራን የሃይማኖት መግለጫ" ለመቀበል የመረጡትን ብቻ ለማደራጀት ቆረጡ፥ ተሳካላቸውም። በልዩ ልዩ ጥያቄዎች አስገዳጅነት የተቀላቀሉአቸውን ወይንም እርዳታቸውን የፈለጉትን ደግሞ ሉተራውያን እያደረጉ አቀፉአቸው። የከምባታ ወንጌላዊት ተፋቾች ለሆኑት 17 አጥቢያዎችም ይህ ዕድል ደረሳቸው። የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የምሥረታ አጀንዳም እ.ኤ.አ. በ1963 ( 1955/56ዓ.ም.) ተዘጋ።

# 4. የሚስዮናውያን መመለስ

በጣሊያን ሹማምንት በወላይታ ታስረው የነበሩ ሰባ ያህል የወንጌል አማኞች መሪዎች ከወኅኒ የወጡት አራት ሺህ ያህል የጣሊያን ሠራዊት ለአርበኞችና ለእንግሊዝ የጦር ኃይል እጁን ሲሰጥ ወኅኒው ያለጠባቂ በሆነበት ዕለት ነበር።[1]

ከነፃነት ትግሉ በኋላ በየዳር አገሩ የነበረው ያለመረጋጋት መልክ እስከሚይዝ ድረስ የመንግሥት መዋቅር በአግባቡ እስከሚዘረጋና አርበኛው ባንዳውና የውስጥ አርበኛው፥ ስደተኛውና ባላገሩ፥ እርስ በርስ አንዱ ሌላውን እስከሚቀበል ድረስ ለወላይታ፥ ለሲዳማ፥ ለከምባታና ሃዲያ ምእመናን የእፎይታ ዓመታት እንደሆኑላቸው በርካታ የሰውና የጽሑፍ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። [2]

---

[1] . Balisky. 1947 p. 183
[2] . Ibid P. 183

ንጉሠ ነገሥቱ በጦርነት የወደመውን ሁለንተናዊ የአገሪቱን ገጽታ እንደገና በአዲስ ይዘት ለማቋቋም አብሮአቸው ለመሥራት የተነሳውን ሁሉ በደስታ ያስተናገዱበትም ይህ ወቅት ነበር።

ቀዳማዊ ኃይለሥለሴ በታሪክ ፊት ሞገስ የሆነላቸው የትምህርትና የጤና ተቋማት የማስፋፋት ፍላጎታቸውን ለማሟላት ለተዘጋጁት ሚስዮናውያን ሁሉ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በጎ ፈቃዳቸውን ሰጡ።[3] ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ጥያቄ ካቀረቡት መካከል ደግሞ ከወረራው በፊት በአገር ውስጥ ሥራ የጀመሩት ቅድሚያ ተሰጣቸው። በአንጻሩም በጣሊያን ወረራ ወቅት ሳይባረሩ የከረሙት የጀርመን ሄርማንስ ቡርግ ሚስዮናውያን ከአገር እንዲወጡ እንደ ተደረገም ልብ ይሏል። ይህ የሚስዮን ድርጅት እንደገና የገባው ከአስር ዓመት ደጅ ጥናት በኋላ ነበር። ቀድሞ በመግባትና ሥራ በመጀመር የተሳካላቸው የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን ሠራተኞች ነበሩ።

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ እንደተገለጸው የኤስ.አይ.ኤም. ዓለም አቀፍ ቢሮ ዳይሬክተር ጋይ ፕሌይፌር በ1935 ዓ.ም. ሐምሌ ወር ላይ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት በቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በምእመናን ትኩስ መንፈስ ተገርመው እንደተመለሱ ሚስዮናውያን እንደገና ወደ አገር የሚገቡበትን ሁኔታ አመቻቹ። እስከ 1937 ዓ.ም. ድረስ ግን የመግቢያ ፈቃድ ለማግኘት አዳግቷቸው ነበር።

በዚህ የተነሣም ከነባሮቹ የሚስዮን ድርጅቶች ዘግይቶ በመግባትና ሥራ በመጀመር ኤስ.አይ.ኤም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል።

ኤስ.አይ.ኤም. ተመልሶ እንደመጣ ያገኘው ትቷት የሄደውን ምስኪን ማኅበርና በጣት የሚቆጠሩ ምእመናን . . . ወዘተ አልነበረም። ቤተ ክርስቲያን ተስፋፍታ፥ ማኅበራዊው ገጽታ ተለውጦ፥ ሁሉም ነገር

---

[3] . Fargher Brain. The Origins Of The New Churches. . .1996 p. 189

በሽግግር ወቅት ላይ ሆኖ እንጂ። የዚህ የሽግግር ወቅት ሁለት ተግዳሮቶች ግን በመጠኑም ቢሆን ሊዘገቡ ይገባል እና እነሆ።

## የመጀመሪያው ተግዳሮት

ሚሲዮናውያን ባልነበሩበትና የኢትዮጵያ መንግሥት በፈረሰበት፥ በጣሊያን የወረራና የስደት ዓመታት ዘመን ተአምራታዊ መስፋፋት ያደረገችውና ራሷን በራሷ ማስተዳደር የጀመረችው ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያም በመንግሥት መመለስ አንጻር፥ ቀጥሎም በሚሲዮናውያን ዳግም ወደ አገር ውስጥ መግባት ምክንያት አዳዲስ አስተሳሰቦችን የማኅበራዊ ግንኙነቶችን እንዲሁም የአስተዳደር ፈሊጦችን ማስተናገድ ግድ ሆነባት። ቤተ ክርስቲያን ከ1928-33 ያለውን ጊዜ ያሳለፈችው ነፍሳትን በመማረክ ላይ እንጂ ላዕላይና ታህታይ መዋቅሮችን በተራቀቀ መንገድ በመዘርጋት ስላልነበረ ከወረራው ማከተም ወዲህ ያጋጠሟት ለውጦች በሁሉም አንጻር ተገዳዳሪ እንጂ ቅን እና ገንቢ አልመሰሏትም። ሊሆንላትም አይችልም። ስለዚህም ያጋጠማትን ተግዳሮት የአስተናገደችው በአያሌው በተከላካይነት መንፈስ ነው።

ድኅረ ወረራ የኢትዮጵያ መንግሥት አገዛዙ በእግሩ ቆሞ አዋጆች፥ መመሪያዎችና ፖሊሲዎች፥ በየፈርጁ ከማእከል መንጭተው በየዳር አገሩ ተግባራዊ እስከሚሆኑ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮና የወንጌል ሥራ ነጻነት ነበራት። በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም. በወላይታ ሶዶ ዙሪያ የነበሩት ሰባ አምስት ያህል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በአንድነት ተሰባስበው እግዚአብሔርን በሙሉ ነጻነት ለማመስገን መቻላቸው ለአባባሉ ዓይነተኛ ማረጋገጫ ነው።[4]

ነገር ግን የመንግሥት መዋቅራዊ ግንባታ እየተጠናከረ በሄደ መጠን የወንጌል አማኞች ነጻነት ቀስ በቀስ ታነቀ። አገር ነጻነቷን በመቀዳጀቷ በእንባ የዘሩትን በደስታ እናጭዳለን ብለው የነበሩት አማኞች ተስፋ

---

[4] Balisky . 1997 p. 200

በነነ። ከወላይታ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ አማኞችና የማኅበር መሪዎች አንዱ የነበሩት አቶ ቶሮ ደቡሽ ለዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እንደተረኩለት፦

*በ1933 ዓ.ም. ጣሊያኖች አስረውኝ ሳለ አለቃቸው ጠርቶ « አንተ በሰላም የምትኖረው እኔ ስሻር ነው፥ . . . » በማለት ወደ ወኅኒ ቤት እንዲመልሱኝ አዘዘ። በሦስተኛው ቀን የእንግሊዝና የአርበኞች ጦር መጥቶ ማረካቸው። ሁላችንም ወኅኒውን ከፍተን ወጣን። አሣሪዎቼ ታሰሩ። " ጦሶ ገለታ ! ጦሶ ገለታ ! . . . የኢትዮጵያን ባንዲራ የመለሰከ አምላክ ጦሶ ገለታ አልኩ ተንበርክኬ። ከጣሊያን በኋላ ስደት የሚነካኝ አልመሰለኝም ነበር። ለካስ ወንጌል ያለመከራ አይሮጥም! ነበር ያሉት ።*[5]

መከራውን ካጸኑት አበይት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች መካከል በፋሽስት አገዛዝ ዘመን ተሸሮ የነበረው የገባር ሥርዓት በድኅረ ነጻነት የፖለቲካ ኃይልን መሠረት ከማጠናከር አንጻር እንደገና መመለሱ ዋነኛው ነው። ድኅረ ነጻነት የእርሻና የመሬት ይዞታ ሦስት ገጽታዎች ነበሩት ይላሉ የታሪክ ተመራማሪው ባህሩ ዘውዴ፦

ባንድ መልኩ ቀደም ሲል የደቡብ ገበሬ በገባርነት ያገለግላቸው የነበሩት ከሰሜን የመጡ ሰፋሪዎች ቀስ በቀስ ከግብሩና ካገልግሎቱ አልፈው መሬቱን በግዥም ሆነ በንጥቂያ የራሳቸው ማድረግ ጀመሩ። ሁለተኛ ለመንግሥት ባለሟሎች በደሞዝ ፈንታ በማደሪያነት የተሰጠው መሬት ከጊዜ በኋላ ወደ ርስትነት ተለውጦ የመንግሥት መሬት ከተባለው እየተቆረሰ ለአገልጋዮቹ(ለመንግሥት) ተሰጠ።[6]

በመሬት ችሮታው ተጠቃሚ የሆኑት አርበኞች፥ ስደተኞች፥ ወታደሮችና ሲቪል ሠራተኞች በአብዛኛው የአካባቢ ተወላጆችና የወንጌል አማኝ ያለመሆናቸውን ያህል ከሞላ ጎደል አነስተኛ ገበሬ በሆነው በሲዳማ፥ በወላይታ በከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያናት ምእመናን ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ያደረጉት ተጽእኖ ተከታታይና የማያቋርጥ ኅሊናንና ሰብእናን የሚያነሳቁል ነበር። ቀዳሚ አማኞች የኢትዮጵያን ባንዲራ

---

5 . ቶሮ ደቡሽ፥ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥ ነሐሴ 1988፥ ሶዶ ወላይታ።

6 . ባህሩ ዘውዴ ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848–1966፥ 1989 ገጽ 200

የመለስክ አምላክ ተመስገን! ባሉበት እንደበታቸው፤ ይህ ግፍ የሚቀጥለው እስከመቼ ነው? ብለው ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት የገጠሙትም ለዚህ ነው። እርሻቸውን ትዳራቸውን ትተው ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ለማቅረብ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መኪና ታልፋለች በተባለበት አውራ ጎዳና ሁሉ እጅ ሲነሱ (ሲሰግዱ) የኖሩት ለዚህ ነው። የደቡብ አርሶ አደሮችንና ነዋሪውን ሕዝብ በልዩ ልዩ መንገድ መሬቱን ከነጠቁት መካከል 80% በላይ ራሶች፥ ደጃዝማቾች፥ ፊታውራሪዎች፥ ቀኛዝማቾች፥ ባላባቶች እና አባ ቆሮዎች ናቸው[7]። ስለዚህም የገባሩን መደብ ሲመቻቸው በመንግሥታዊው መዋቅር በኩል ወይንም በተለያዩ ስያሜዎች በሚታወቀው ልማዳዊ ( ለምሣሌ ሴራ) ሥርዓት መሣሪያነት ማስጨነቃቸው አይቀሬ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ስለ ወንጌል ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ካሰባሰበቻቸው ምእመናን መደባዊ ዳራ ሳቢያ እንደማንኛውም የኅብረተሰብ አባል ይህን የመከራ ጽዋ ስትጎነጭ ኖረች።

በጣሊያን ወረራ ወቅት በመከራው እቶን መካከል አልፎ በድኅረ ነጻነት እፎይታን እጎናጸፋለሁ ብሎ ተስፋ ያደረገውን የወንጌል አማኙ ማኅበረሰብ ግራ ያጋባ ይህ መላቅጥ የሌለው የመሬት ሥርዓት እስከ 1967ዓ.ም. ድረስ ተጣብቆበት ቆዬ። አእምሮውና ኅሊናው በወንጌል የበራለት ምእመን፤ ስለ ገባሮቹ፥ ስለ መሬቱ ስሪት፥ እግዚአብሔር በፈጠረለት ምድር ላይ ስላለው መብት የሚናገረው እውነት ያለው ሕዝብ፥ በመሬት ከበርቴዎች የተጫነበት ቀንበር በ1967 ዓ.ም. ሲሰበር ባለመሬት ያረገውን አብዮት እንደ ጸሎቱ መልስ አርጎ መቀበሉ እንዲሁም ከእምነቱ ተጻራሪ ሆኖ እስኪገለጥበትም ድረስ ያለ መቆጠብ ( ሚዛን ሳይጠብቅ) አብዮቱን ለመደገፍ ያበቃው ይህ ነበር ለማለት ያስደፍራል።

---

[7]. Eide, Oyvind M. Revolution And Religion In Ethiopia. 1995 p 31, 32